# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
# የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት

# የ3 ዓመት (ከ1996-1998ዓ.ም.)
# የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ስትራቴጂካዊ
# እቅድና ሥራ አመራር ሰነድ

ግንቦት 1995ዓ.ም.

ባሕር ዳር

<u>ማ ው ጫ</u>

<u>ርዕስ</u> <u>ገጽ</u>

ማጠቃለያ

መግቢያ

1. የኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ አጠቃላይ ገጽታ

1.1 የስርጭት አድማስ.......................................................................... 6

1.2 እስካሁን የተደረጉ ጥረቶች.......................................................... 6

1.2.1 በብሔራዊ ደረጃ.............................................................. 7

2. የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆጣጠሪያ ምክር ቤት............................ 9

2.1 የሴክሬታሪያቱ አደረጃጀት........................................................... 10

2.2 የተቋቋመበት ዓላማ ..................................................................... 10

2.3 በክልሉ ያጋጠሙ ችግሮች .......................................................... 11

2.4 በክልሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭትን የሚያባብሱ ሁኔታዎች....... 13

3. የተግባርና ኃላፊነት ትንተና /Mandate Analysis /............................................. 13

4. የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት ራዕይ፣ተልዕኮና እሴቶች.....

4.1 ራዕይ/Vision.......................................................................... 14

4.2 ተልዕኮ /Mission...................................................................... 14

4.3 ዕሴቶች/Values........................................................................ 15

5. ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ትንተና.................................................... 16

6. የሁኔታዎች ትንተና............................................................................... 22

6.1 ውጫዊ ሁኔታዎች..................................................................... 22

6.2 ውስጣዊ ሁኔታዎች.................................................................... 25

7. የስትራቴጂክ እቅድና ሥራ አመራር ግቦችና ዓላማዎች....................................... 26

8. የቁልፍ ጉዳዮች ትንተና.......................................................................... 30

9. የማስፈፀሚያ ስልቶች/ስትራቴጂዎች/.......................................................... 33

10. የ1996-1998 የሥራ መርሀ ግብር.............................................................. 35

11. የሰው ኃይል እቅድ መርሀ ግብር.............................................................. 41

12. የፋይናንስ እቅድ መርሀ ግብር.................................................................. 42

13. ክትትልና ግምገማ............................................................................... 43

14. የተያዙ ታሣቢዎችና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶች .......................................... 44

## ማጠቃለያ

የአማራ ብሄራዊ ክልል ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ከተቋቋመበት ከ1993 ዓ.ም. ጀምሮ በአዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ሀላፊነቶች በብቃት ለመወጣት የሀገሪቱን ስትራቴጅካዊ መርሃ-ግብር በመመርኮዝና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ፣ ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራትን በመለየት የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የልማት እቅድ እያዘጋጀ ሲተገብር ቆይቷል።

በአሁኑ የ3 ዓመት ስልታዊ እቅድ ውስጥ በክልሉ ውስጥ በዋናነት ሊፈፀሙ ይገባቸዋል የተባሉ ተግባራትና ግቦች ተካተዋል እንዲሁም ለተግባራቱ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገው የበጀትና የሰው ሃይል ፍላጎት እንዲታይ ተደርጓል። በዚህ መሰረት በሚቀጥሉት 3 ዓመታት የአብክመ ኤችአይቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት የሚከተሉትን አበይት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ይሰራል፡-

- የተቀናጀ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የህብረተሰብ አቀፍ ተቃማት፣ እንዲሁም የግለሰቦችንና ድርጅቶችን የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴና ተሳትፎ ለማሳደግ፣
- በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግና አቀናጅቶ ለመምራት፣
- ያላሰለሰና ተከታታይነት ያለው የመከላከል ትምህርት በመስጠት የክልሉ ህብረተሰብ የባህሪይ ለውጥ እንዲያመጣና ራሱን ከኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረስ ጠብቆ ዘላቂ ልማቱን እንዲያፋጥን ለማገዝ፣
- በክልሉ ውስጥ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ሰዎችና ወላጅ አልባ ህፃናት የሚደረገውን የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ለማጠናከር፣
- በክልሉ ውስጥ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና ወላጅ አልባ ህፃናት ሰብዓዊ መብት የተከበረ እንዲሆን ለማድረግ፣
- በክልሉ ውስጥ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚደረጉ የጥናትና የምርምር ስራዎችን ለማበረታታት፣
- በክልሉ ውስጥ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል የሚውል በቂ ሃብት ለማፈላለግና በሚገባ ጥቅም ላይ ለማዋል፣
- ከክልል እስከ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን የሚገኘውን የሴክሬታሪያቱንና የአጋር ድርጅቶችን የሰው ሃይል የመፈፀም አቅም ለመገንባትና፣
- በአጠቃላይ በክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር የሁሉም ዜጋ ድርሻ መሆኑ ታውቆ ተገቢው የጋርዮሽ ርብርብ እንዲደረግበት ለማስቻል ነው።

የአማራ ብሔራዊ ክልል ሀገራዊ በሆነው መረጃ መነሻነት በኤች አይ ቪ/ኤድስ በእጅጉ እየተጠቃ ያለ ክልል ነው፡፡ ይህም ወረርሽኙ አምራች የሆነውን የሰው ኃይል የሚያጠቃ ከመሆኑ አንፃር አስጊ ሁኔታ የሚደቅን ነው፡፡ የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ይችል ዘንድ ሁሉንም ወረዳዎች የሚሸፍን እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም መነሻ የሆነው በኘሮጀክት ወረዳዎች እስካሁን የተደረገው እንቅስቃሴ እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑና የገንዘብ አጠቃቀማችንም አነስተኛ መሆኑ ሲሆን የክልሉ ኅብረተሰብ የተጋረጠበትን ችግር መክቶ የጀመረውን የልማት እንቅስቅሴ ከግብ ለማድረስ ይችል ዘንድ ከእስካሁኑ እንቅስቃሴ በስፋትም ይሁን በጥልቀት የተለየና ሁሉንም ኅብረተሰብ የሚያሳትፍና የሚሸፍን ለማስመዝገብ የሚያልመውም ግብ ጉልህ መሆን እንደሚገባው ያምናል፡፡

በመሆኑም የሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤት የተጠቀሱትን ዓላማዎች በእቅድ ዘመኑ ለማሳካት ብር 146,119,520 እንደሚያስፈልገው የታቀደ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ብር 5,666,842 የሚሆነው ከመንግስት የሚሸፈንና ብር 140,452,678 ያህሉ ደግሞ ከውጪ ብድርና እርዳታ እንዲሁም ከመያድና የግል ተቋማት የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ከሰው ሃይል አኳያም በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ሴክሬታሪያቱ በየደረጃው ባሉ ጽ/ቤቶቹ 144 ሠራተኞች የሚኖሩት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 53 የወረዳ አስተባባሪዎች በአቅም ግንባታ ጽ/ቤት የሚቀጠሩ ይሆናሉ፡፡

በስልታዊ የእቅድ ዶክመንቱ የተመለከቱት ዝርዝር ተግባራት በትክክል ለመፈፀማቸውም ሴክሬታሪያቱ ተገቢ ነው ያለውን የክትትልና ግምገማ ስርዓት አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት እያንዳንዱ ተግባር በመርሀ-ግብሩ እንደተመለከተው የመለኪያ መስፈርት እንዲቀመጥለት የተደረገ በመሆኑ በእቅድ ዘመኑ ወቅትም ይሁን በማጠቃለያው ለሚደረገው የአፈጻጸም ግምገማ አመቺ ነው የሚል እምነት አለን፡፡

## መግቢያ

የተሻሻሉ የአሠራር ሥልቶችን መዘርጋትና የተቀላጠፈ አገልግሎት መሥጠት ለፈጣን ዕድገት መሠረት በመሆናቸው አገልግሎት አሠጣጡ ጥራት ያለውና የተቀላጠፈ እንዲሆን የሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትም በክልሉ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ለማምጣት ነባራዊውን የተንዛዛ የአገልግሎት አሠጣጥ ጥራት ያለውና ውጤት በሚያመጣ መልኩ መከናወን እንደሚገባው በማመን ከመቼውም የበለጠ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

የክልሉ ሕብረተሰብ የተቀላጠፈና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኝ አገልግሎት ሰጪ መንግስታዊ ድርጅቶች በዕቅድ የሚንቀሳቀሱና የማስፈፀም አቅም እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ የአቅም ግንባታ ቢሮ የሲቪል ሠርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሙ ዕውን እንዲሆን የመንግስት ድርጅቶችን አቅም ለማጎልበት እንቅስቃሴውን በስፋት ጀምሯል፡፡ የዚህ ማሻሻያ ኘሮግራም አንዱ አካል የመንግስት ድርጅቶች በመጪዎቹ 3 ዓመታት በሥራ ላይ ሊውል የሚችል ስትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥራ አመራር ቀርፀው መንቀሣቀስ እንዲችሉ የስትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥራ አመራር ዝግጅት ሥልጠና በማዘጋጀት የመንግሥት ድርጅቶች ኃላፊዎችና ተወካዮች እንዲሠለጥኑ አድርጓል፡፡ በዚህ ሥልጠና የክልሉ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሴክሬታሪያት ተሣታፊ በመሆኑ በመጪዎቹ ሶስት ዓመታት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኝን ለመግታት የሚያስችል ሰትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥራ አመራር በመቅረጽ ላይ ይገኛል፡፡
የስትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥራ ዓመራር ዝግጅት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሴክሬታሪያት ከተመሠረተ ጊዜ አንስቶ በአይነቱም ሆነ በአሠራሩ የመጀመሪያ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የነበረው ግንዛቤ በሌሎች የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንደነበረው ዓይነት ኘሮጀክቶችን በመቅረጽ በተግባር ለመፈፀም የተመሠረተ ባለመሆኑ ዕቅድ አውጥቶ መንቀሣቀስ የሚቻል አይደለም በሚል አስተሳሰብ የተቃኘ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ነገር ግን አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም ሆኑ ለማስተባበር የተቋቋሙ ደርጅቶች የሚሠጡት አገልግሎትና ድጋፍ የተቀላጠፈና ጥራት ያለው እንዲሆን አቅደውና የማስፈፀሚያ ስልቶችን ነድፈው መንቀሳቀስ እንደሚገባቸው በተጨባጭ ታይቷል፡፡

በዚህ መሠረት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሴክሬታሪያትም በመጪዎቹ ሶስት አመታት ለአጋር ድርጅቶቹም ሆነ ለሕብረተሰቡ የተቀላጠፈና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት፣ በማስተባበርና በማቀናጀት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ውጤት ሊያመጣ የሚያስችል ርብርብ ለማድረግ ይህን የ3 ዓመት ስትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥራ አመራር ሰነድ አዘጋጅቷል፡፡

## ዓላማ

- ጉዳዩ የሚመለከታቸው በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የተሠማሩ ወይም አካተው የሚሠሩትን አካላት ፍላጎት በማካተት በተሻለ ርብርብ እና ቅንጅት የወረርሽኙን ሥርጭት ለመግታት፣
- በየደረጃው ያሉ ሴክሬታሪያት በየአካባቢያቸው ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመንተራስ የየበኩላቸውን ዕቅድ እንዲቀርፁ በማድረግ በሽታውን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ሕብረተሰቡ የተሳተፈበት ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት፣
- በኤች አይ ቪ/ኤድስ ለተያዙና ለተጠቁ ሰዎች አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ ለማድረግና አድልዎንና መገለልን ለማስወገድ፣
- በመጪዎቹ 3 ዓመታት ውስጥ ሀብትን በአግባቡና ለታለመለት ዓላማ በማዋል የኅብረተሰቡን የባህሪይ ለውጥ የሚያፋጥኑ ውጤታማ ሥራዎችን ለማከናወን
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመግታት በሚደረገው ርብርብ በተሻለ አደረጃጀት ሁሉንም መንግስታዊ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሕብረተሰብ አቀፍ ተቋማት፣ /ዕድር፣ ክበባት፣ ማህበራት/ የሀይማኖት ተቋማት ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩና ወላጅ አልባ ሕፃናት ማህበራትን በማቀናጀት በተባበረ አቅም የወረርሽኙን ሥርጭት መግታት ዋና ዋና አላማዎች ናቸው::

## የዶክሜንቱ አሠራር ሂደት

የዚህን ስትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥር አመራር ዝግጅት የተሣካ ለማድረግ ሴክሬታሪያቱ የዕቅድ ዝግጅት ኮሚቴ አቋቁሟል:: በአብክመ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት የስትራቴጂክ ዕቅድና ሥራ አመራር ሥልጠና ተካፍለው የመጡ ሁለት የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች የዕቅድ ዝግጅት ኮሚቴ እንዲሆኑ ተወስኗል:: የስትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥራ አመራር ሰነዱ በየደረጃው ባሉ ጽ/ቤቶች መዘጋጀት ስለነበረበት የዕቅድ ኮሚቴው በየደረጃው ያሉ ጽ/ቤት አስተባባሪዎችን በመጋበዝ በሰነዱ አዘገጃጀት ላይ ዐውደ ጥናት አካሂዷል:: በዚህ ዐውደ ጥናት ላይ የክልሉ ሴክሬታሪያት ባለሙያዎች የዞን አስተባባሪዎች፣ በፕሮጀክት የታቀፉ ወረዳዎች በአቅም ግንባታ የተቀጠሩ የወረዳ አስተባባሪዎች በጠቅላላው 50 ተሣታፊዎች ለሁለት ቀናት ያክል በተካሄደው ዐውደ ጥናት ተካፋይ ሆነዋል::

በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚዘጋጀው ስትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥራ አመራር የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ መነሻ ማድረግ ስለሚገባው በቅድሚያ የክልሉ ሴክሬታሪያት መነሻ ሰነድ ማዘጋጀት ነበረበት:: በመሆኑም ለመነሻ ሰነዱ የሚሆን በዕቅድ ኮሚቴው በኩል ለ60 አጋር ድርጅቶች መጠይቅ በማዘጋጀት የተሰራጨ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 40 የሚሆኑትን ምላሽ አግኝተናል:: የነዚህን አጋሮች ፍላጎት በማካተት በክልሉ ሴክሬታሪያት ባለሙያዎች ሙሉ ተሣትፎ የ3 ዓመታት ስትራቴጂካዊ ዕቅድና ሥራ አመራር መነሻ ሰነድ በጋራ ከተዘጋጀ በኋላ ለወረዳዎች የተላከ ሲሆን የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት

ውስጥ በማስገባት ወረዳዎች ያዘጋጁትን ሠነድ በመመርመር፣ ከአቅምና ከሀብት ጋር በማገናዘብ ይህ ስትራቴጂካዊ የሥራ አመራር ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም

ከ1996ዓ.ም. ጀምሮ በቀጣዮቹ 3ዓመታት የክልሉን የኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር የሚመራ ይሆናል።

# 1. የኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ አጠቃላይ ገጽታ

## 1.1 የስርጭት አድማስ

የኤች አይ ቪ/ኤድስ በአሁኑ ጊዜ በሰው ልጅ ሕልውና ላይ ያንዣበበና በገዳይነቱ በዓለም ላይ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት በሽታ ነው። ወረርሽኙ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 20ዓመታት በሰው ልጆች ላይ እያደረሰ ያለው እልቂት ያስከተለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ድቀት እጅግ አስከፊ ነው።

በቅርብ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ወረርሽኙ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ 45ሚሊዮን ሕዝብ በቫይረሱ ሲያዝ ከ21.8 ሚሊዮን በላይ ደግሞ ለሕልፈተ ሕይወት ተዳርገዋል። ከዚህ ውስጥ 3.8 ሚሊዮን ሕፃናት መሆናቸው በሽታው ምን ያህል አስከፊ ደረጃ ላይ እንደደረሰ መረዳት ይቻላል።

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ በድሀው የአፍሪካ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ዕልቂት በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። በተለይም ከሠሀራ በታች ያሉ አገሮች ላይ ወረርሽኙ እያደረሰ ያለው ሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ከመቸውም በላይ በመሆኑ ከማንኛውም ጉዳይ የበለጠ ትኩረት የሚሻ ሆኗል። በአለም ላይ በቫይረሱ ከተያዙ ሰዎች 25 ሚሊዮን የሚሆኑትና ለሕልፈተ ሕይወት ከተዳረጉትም 17 ሚሊዮን የሚሆኑት ከሰሀራ በታች ባሉ አገሮች ውስጥ የሚገኙ መሆኑና የቫይረሱ ስርጭትም ወደ 20% መድረሱ በፍጥነት እየተዛመተ ለመሆኑ አመልካች ነው።

ከሰሀራ በታች ከሚገኙ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ በእጅጉ ከተጠቁ አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት። በቫይረሱ ስርጭት ኢትዮጵያ በዓለም 16ኛ ደረጃን ስትይዝ በኤድስ ሕሙማን ቁጥር ብዛት ከደቡብ አፍሪካ እና ከናይጀሪያ ቀጥላ 3ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በገጠራቱ ኢትዮጵያ ከ15-49ዓመት እድሜ ክልል ከሚሆነው ከ13ቱ አንዱ ፣ በከተሞች ደግሞ ከ6ቱ አንዱ ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ታውቋል። ሀገራዊ የቫይረሱ ስርጭት 7.3% የደረሰ ሲሆን በአንዳንድ ከተሞች ግን እስከ 22.3% እንደሚደርስ ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህም ሀገራዊ የቫይረሱ ስርጭት በከተሞች 13.7 በገጠር ደግሞ 3.7 እንደሆነ ያመላክታል። በቫይረሱ የተያዙት ዜጎችም 1.2 ሚሊዮን እንደሚደርሱና ከዚህ ውስጥ 250,000 የሚሆኑት ህፃናት ናቸው። በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ከ750,000 በላይ ህፃናት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ሳቢያ ወላጅ አልባ መሆናቸውም በዚሁ ጥናት ተረጋግጧል።

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭት እያስከተለ ካለው የሰብዓዊ ዕልቂት ባሻገር በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴም አሉታዊ ተጽዕኖው በእጅጉ የከፋ ሆኗል፡፡ ወረርሽኙ በብዛት የሚያጠቃውም አምራች ኃይል የሆነውን ወጣቱን የሕብረተሰብ ክፍል በመሆኑ የምርት መቀነስ እያስከተለ ይገኛል፡፡ የነፍስ ወከፍ ገቢን ከ8-13% በዓመት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ሕክምና፣ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልገው ወጪ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ የቤተሰብ ገቢን እንዲያሽቆለቁል ከማድረግ አልፎ፣ ኢንቨስትመንትን ያዳክማል፡፡ ሕፃናትን ያላሳዳጊ አረጋውያንን ያለጧሪ ያስቀራል፡፡ በመሆኑም በሽታው ምን ያህል በዕድገታችን ላይ እያንዣበበ ያለ አደጋ መሆኑን መገመት አያዳግትም፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልል ደረጃም ምንም እንኳ የተቀናጀ መረጃ ባይኖርም በአንዳንድ መረጃ ማሰባሰቢያ እንዲሆኑ በተመረጡ ቦታዎች የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የቫይረሱ ስርጭት ከሀገራዊ ሁኔታ እምብዛም የተራራቀ አይደለም፡፡ ከዚህም አንፃር የቫይረሱ ስርጭት 7.3% እንደሆነና የክልሉ ዋና ከተማ ባሕር ዳር በቫይረሱ ተጠቂነት በሀገሪቱ ካሉት ከተሞች በቀዳሚነት /23.4%/ የምትገኝ ሲሆን ከኗሪው ሕዝብ አንፃር ሲሰላ በክልሉ 750,000 ወገኖች ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ለመሆናቸው ፍንጭ ይሠጣል፡፡

## 1.2 እስካሁን የተደረጉ ጥረቶች

### 1.2.1. በብሔራዊ ደረጃ

በሽታውን ለመከላከልና ጉዳቱን ለመቀነስ መንግሥት ሁለት የመካከለኛ ጊዜ ዕቅዶች እ.ኤ.አ ከ1987-1996ዓ.ም.አውጥቷል፡፡ ዕቅዶቹ በተለይ በሕብረተሰቡ ደረጃ በቂ ተሣትፎ ስላልነበራቸው ግባቸውን መምታት አልቻሉም፡፡ በአገልግሎት ሰጭዎችም መካከል በቂ ቅንጅታዊ አሠራር አልነበረም፡፡ ስኬታማ ፕሮግራሞችና በመስኩ በቂ ልምድ ያላቸው አገልግሎት ሰጪዎች ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ የበሽታውን ሥርጭት በመግታት በኩል በቂ አስተዋጽኦ ለማድረግ አልቻሉም፡፡

በዚህ ምክንያት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኙም አስከፊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ መንግሥትም የመንግሥስት ሴክተሮችና ሕዝቡ በአንድ ላይ እንዲነሱና በቅንጅት ለመንቀሳቀስ የሚረዳና ለእንቅስቃሴው ሁኔታዎችን የሚያመቻች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፖብሊክ ብሔራዊ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፖሊሲ በነሀሴ ወር 1990 /እ.ኤ.አ ኦገስት 1998/ አውጥቷል፡፡ በመቀጠ ልም ዘርፈ ብዙ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ኘሮጀክት ለመንደፍ ሥራ ላይ ያዋለ ሲሆን የዚሁ የኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ኘሮጀክት መሠረታዊ ዓላማ የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ ሥርጭትን ለመቀነስና በኤች አይ ቪ/ኤድስ ለተያዙና ለተጠቁ ሰዎች አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ ለማድረግ እንዲቻል ሁኔታዎችን ማመቻቸትና የቴክኒክና የገንዘብ እገዛ መስጠት ነው፡፡ የኘሮጀክቱ ልዩ ትኩረት የበሽታውን ሥርጭት ለመግታት አገር አቀፍ ተነሣሽነትን ማበረታትና ምላሹን መደገፍ ነው፡፡ ኘሮጀክቱ መንግሥት ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከ2000ጠ2004 ላወጣው

መርሀግብር 63.4ሚሊዮን ዶላር የመደበ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከ28ሚሊዮን ዶላር በላይ ሕብረተሰቡ በራሱ ተነሣሽነት ለሚያደርገው ፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የሚውል ነው።

የኘሮጀክቱ የመጀመሪያ ዓመት ጥረት በሽታውን ለመቀነስና ለማስወገድ እየተደረጉ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ይበልጥ በማስፋፋትና በማሣደግ እንዲሁም በማዕከል ደረጃ ዕቅድ የማውጣት የማስፈፀምና የመከታተል አቅምን በመገንባት ላይ የሚያተኩር ሲሆን የኘሮጀክቱ የሁለተኛና ሦስተኛ ዓመት ዕቅድ ደግሞ በተገኙ ተጨባጭ ውጤቶችና ልምዶች ላይ በመመርኰዝ አድማሱን ይበልጥ ማስፋፋት ይሆናል።

- በብሔራዊ ሴክሬታሪያቱ በተነደፈው የዘርፈ ብዙ ኤድስ መከ/ኘሮጀክት 173 ወረዳዎች የሚታቀፉ ሲሆን ለዚሁ ሥራ ፈንድ ይለቃል፣ በቀጣይ የወረዳዎችን ፈንድ ያፈላልጋል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱትን ይደግፋል።

ይህን መነሻ በማድረግ የአብክመ የጤና ፖሊሲ ቀርጿል። ይህ ፖለሲ በመከላከል ተግባር ላይ ያተኮረ በመሆኑ፤ በሀገራችን የተነደፉ የመከላከልና ቁጥጥር ተግባራት በክልላችንም ትኩረት ሰጥተን የምናከናውናቸው ይሆናል።

በሽታውን በመከላከል ረገድ ቅድሚያ ትኩረታችን ጤናማው ሕብረተሰብ ስለበሽታው በቂ ግንዛቤ ኖሮት የባሕሪ ለውጥ እንዲያመጣ የተለያዩ የቅስቀሳና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ማከናወን በመሆኑና ይህም ጉዳይ በጤና ዘርፍ አደረጃጀታችን ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ሁሉንም ኃይሎች ማንቀሳቀስ የሚጠበቅብን ይሆናል።

በዚህ አንፃር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በየደረጃው የተቋቋመው የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ም/ቤትና ሴክሬታሪያት አደረጃጀቶች አማካኝነት በዘርፉ የሚደረገውን ጥረት በማስተባበርና አስፈላጊ የሆነ ሀብትን በማፈላለግ ረገድ ሰፊ ድርሻ አላቸው።

በመሆኑም በተደራጀ አኳኋን በሽታውን ለመከላከል ፍላጎት ያላቸው የመንግሥት ተቋማት፣ የማሕበረሰብ ክፍሎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ግለሰቦች፣ ወዘተ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በሙያና በገንዘብ በማገዝ በመከላከል ሥራ ላይ በስፋት እንዲሳተፉ የሚደረግ ይሆናል። በመንግስትም ሆነ በግል ድርጅቶችም የላቦራቶሪና የምክር አገልግሎት እንዲስፋፋ አስፈላጊ የባለሙያ፣ የመድሃኒት፣ የላቦራቶሪ ዕቃዎች አቅርቦትና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን እንዲሟሉ ጥረት ይደረጋል።

ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴ ቅንጅታዊ አሠራርን የተከተለ እንዲሆን ከዓለም ባንክ በተገኘው የባለዘርፈ ብዙ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ፈንድና ከሌሎች ለጋሾች በሚገኝ የብድር ገንዘብ ድጋፍ

ሁሉን አቀፍ የሆነ የመከላከል ተግባር ተጠናክሮ የሚመራበትን አካሄድ በትኩረት የምናከናውነው ይሆናል።

ከ1993-1997 የተነደፈው ብሔራዊ የጤና ፖሊሲ በአንፃሩ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኙን ለመከላከል ሌላው ምቹ ሁኔታ ነው። ይህ ፖሊሲ ስድስት ዓላማዎችን ያካተተ ሲሆን እነርሱም፦

1. በአገሪቱ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ፣
2. ኤድስ በሕሙማንና በአገሪቱ ላይ ለያደርስ የሚችለውን ስነ ልቦናዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቋቋም የብዙ ዘርፎችን የተባበረ ጥረትና እንቅስቃሴ የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንን የጋራ ጥረት አስተባብሮ በመንቀሣቀስ ለበሽታው መከላከልና የሰው ኃይል አቅም እንዲገኝ ማድረግ፣
3. ከቫይረሱ ጋር ለሚኖርና ለኤድስ ሕሙማን፣ በኤድስ ሳቢያ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆችና ረዳት የሌላቸው የሕሙማን ቤተሰብ አባላት የጤና እንክብካቤ የስነ ልቦና ምክርና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት።
4. ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩና ለኤድስ ሕሙማን ሰብዓዊ መብታቸው የተከበረ እንዲሆንና በሕብረተሰቡም ዘንድ ምንም ዓይነት ልዩነት የማይደረግባቸው መሆኑን ማረጋገጥ።
5. ሴቶች ወጣቶችና ሌሎች ለበሽታው ይበልጥ የተጋለጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች ራሣቸውን ከበሽታው ለመከላከል እንዲችሉ የመወሰን መብትን ተግባራዊ የማድረግ አቅም እንዲኖራቸው ማድረግና
6. ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከል በማከምና በሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት ላይ ያተኮሩ የምርምርና ስርፀት ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ናቸው።

በአጠቃላይ በክልሉ የበሽታውን ሥርጭት ለመግታት በምናደርጋቸው ጥረቶች በመርህ ግብሩ ማጠናቀቂያ በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎችን ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ መቶኛ እንዲቀንስና በኮንዶም አቅርቦታችንም የኮንዶም አጠቃቀም 80 በመቶ እንዲደርስ ጥረት የሚደረግ ይሆናል።

## 2. የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ምክር ቤት

የሀገር አቀፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ም/ቤት አመሠራረትን ተከትሎ የአብክመ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 73/1994ዓ.ም. ተቋቁሟል። ም/ቤቱ የሥራ አመራር ቦርድና የዕለት ተዕለት ተግባሩንም የሚያከናውን ሴክሬታሪያት አቋቁሟል። በየደረጃው በዞን በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ም/ቤት በማቋቋም በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያመች መዋቅር ዘርግቷል።

## 2.1 የሴክሬታሪያቱ አደረጃጀት

በአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 73/1994ዓ.ም. መሠረት የም/ቤቱ ሴክሬታሪያት በክልል ደረጃ የተቋቋመ ሲሆን፡፡ በዞንና በወረዳ ደረጃም የማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል፡፡

## 2.2 የተቋቋመበት ዓላማ

- ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴ በተቀናጀና በተባበረ አሠራር ላይ ተመስርቶና ተጠናክሮ እንዲካሄድ በማድረግ የክልሉ ሕብረተሰብ እራሱን ከወረርሽኙ እንዲጠብቅና ለኤድስ በሽታ እንዳይጋለጥ በመከላከል ለቀጣይ የዕድገት ጉዞው አስተማማኝ መሠረት መጣል፡፡
- በኤድስ ሳቢያ በክልሉ ውስጥ እየደረሰ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቦናዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ፡፡

የመስሪያ ቤቱን የሰው ኃይል በተመለከተ፣ ኃላፊውን ጨምሮ 7 የቴክኒክ ባለሙያዎች እንዲሁም 10 የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ይዞ የተዋቀረና የሚንቀሳቀስ ሲሆን ዝርዝሩም፣

- የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ ...................................... 1
- የግምገማና ክትትል ባለሙያ.......................... 1
- የስል/ማኅ/አገ/ፓር/መምሪያ ኃላፊ..................... 1
- የአክሽን አይድ ሲፓ ኘሮጀክት ኦፊሰር............ 1
- የፋይናንስ ኦፊሰር........................................... 1
- ረዳት ፋይናንስ ኦፊሰር.................................. 1
- ረዳት ኘሮጀክት ኦፊሰር.................................. 1
- ገንዘብ ያዥ..................................................... 1
- ንብረት ክፍል ............................................... 1
- ፀሐፊ............................................................. 2
- ሾፌር............................................................. 2
- ተላላኪ ......................................................... 1
- ጥበቃ............................................................ 2
- ጽዳት............................................................ 1

በዞን ደረጃ በ11 ዞኖች አንድ የዞን ሴክሬታሪያት አስተባባሪ በዞኑ አስተዳደር ቢሮ ውስጥ በመሆን እንዲሁም በወረዳ ደረጃ በ20 የኘሮጀክት ወረዳዎች አንድ የወረዳ አስተባባሪ በወረዳው አስተዳደር ቢሮ ውስጥ በመሆን ያስተባብራሉ፡፡ ከኘሮጀክት ውጭ ባሉ ወረዳዎች የአቅም ግንባታ ቢሮ ተጨማሪ የወረዳ አስተባባሪዎችን በመቅጠር ሽፋኑን በማስፋት ላይ ይገኛል፡፡ እስካሁንም ባለው ጊዜ ከ13

የማያንሱ የወረዳ አስባባሪዎች ተቀጥረው የተመደቡ ሲሆን አነስተኛም ብትሆን ከመንግስት በጀት በሚደረግላቸው ድጋፍ መጠነኛ ሊባል የሚችል እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ሴክሬታሪያቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በተሰጠው ስልጣን እና ኃላፊነት መሠረት የኤች አይ ቪ/ኤድስን ሥርጭት የመቆጣጠርና የመከላከል ተግባራትን እየፈፀመ ይገኛል። ሴክሬታሪያቱ በክልሉ የሚንቀሣቀሱ መንግስታዊ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሀይማኖትና የሕብረተሰብ አቀፍ ተቋማት፣ ፀረ ኤድስ ክበባትን፣ ዕድሮችንና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና /ወላጅ አልባ ሕፃናት ማኅበራት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በመደገፍ የበኩሉን በማከናወን ላይ ነው።

እስካሁን ባለው ጊዜ ከUNICEF በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ 18 ለሚሆኑ መያድ ብር 3,583,869.00 የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ድርጅቶቹ የተለያዩ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ተግባር እንዲያከናውኑ አድርጓል። እንዲሁም በኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ኘሮግራም ሁሉም መንግስታዊ ድርጅቶች ከመደበኛ ሥራቸው ጋር ኤች. አይ.ቪ/ ኤድስ የመከላከል ተግባር አካተው እንዲሠሩ የሚጠበቅ በመሆኑ 20 ለሚሆኑ የመንግስት ሴክተሮች ብር 617,000.00 በሚሆን ገንዘብ ያቀረቡትን ኘሮፖዛል በመገምገምና ድጋፍ በማድረግ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሥራ ቦታ ለመከላከል /Work place intervention/ የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ተሞክሯል።

ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች/ወላጅ አልባ ሕፃናት ማህበር እንዲቋቋም በተደረገው ጥረት በክልሉ በሁለት ዞኖች ማህበራት ተቋቁመዋል። ለነዚህ ማህበራት አስፈላጊውን የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ፈንድ /አምሣኘ/ 18 ወረዳዎች፣ እንዲሁም በአክሽን ኤይድ/አ.ኤ.ኢ/ 2 ወረዳዎች በጠቅላላው 20 ወረዳዎች በማቀፍ እነዚህ ወረዳዎች ባቀፏቸው ቀበሌዎች በተለይ የወላጅ አልባ ሕፃናትና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ድጋፍ እና እንክብካቤ እንዲጠናከር በማድረግ ላይ ይገኛል።

ሴክሬታሪያቱ ፈንድ የማፈላለግ ጥረቱን በመቀጠል በተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ ወረዳዎችን በማቀፍ ለመሥራት ያሣዩትን ፍላጎት በመቀበል በመጪዎቹ ዓመታት በተጨባጭ የሚታወቅ በሲዊድን ተራድኦ በምስ/ጎጃምና በደ/ወሎ ዞኖች የሚገኙ 16 ወረዳዎች በተባበሩት መንግስታት የልማት ኘሮግራም በክልሉ ምግብ አጠር የሆኑ 16 ወረዳዎች ውስጥ የፀረ ኤድስ ሥራዎች እንደሚደገፉ ቃል ተገብቷል። እንዲሁም የኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የኤድስ መከ/ኘሮጀክት ተጨማሪ 12 ወረዳዎችን ለማቀፍና በአክሽን ኤድ ኢትዮጵያ ተጨማሪ 3 ወረዳዎችን ለማካተት ቅድመ ዝግጅቱ ተጠናቋል።

## 2.3 በክልሉ ያጋጠሙ ችግሮች

ሴክሬታሪያቱ በክልል ደረጃም ሆነ በየደረጃው ባሉ ጽ/ቤቶቹ የሥራው ሥፋት ከሚጠይቀው አኳያ በተሟላ የሠው ኃይል አለመደራጀቱ ሊጨበጥ በታሰበው ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አስከትሏል፡፡ በተለይ በተለያዩ አካላት የሚቀርቡ ኘሮጀክት ኘሮፖዛሎች የሚገመገሙት በክልሉ በተቋቋመው ገምጋሚ ቦርድ ሲሆን ቦርዱ በየጊዜው እየተሰበሰበ በሚፈለገው መጠን ኘሮጀክቶችን መገምገም ባለመቻሉ ምክንያት የብዙዎቹ ድርጅቶች ጥረት እንደተሰተጓጐለ ይገኛል፡፡ በቅርቡ ይህን አሠራር ለማሻሻል ከብሔራዊ ሴክሬታሪያት ጋር ስምምነት ላይ የተደረሰ በመሆኑ ወደፊት በዚህ ረገድ የተቀላጠፈ አሠራር ሊኖር እንደሚገባው ታምኗል፡፡

የኘሮጀክት አተገባበርን በተመለከተ ብዙዎቹ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በቅስቀሣ ሥራ ላይ የተመሠረቱ እንጂ የባህሪ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ ባለመቀየሳቸው በሕብረተሰቡ ዘንድ ተጨባጭ ለውጥ አልታየም፡፡ በቅርብ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተካሄደ ጥናት ከ95% በላይ የሚሆነው የሕብረተሰብ ክፍል ስለበሽታው መተላለፊያ መንገዶች እንደሚያውቅ ነገር ግን የባህሪ ለውጥ አለማምጣቱን ማሳየቱ ወደፊት የባሕሪ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው በሰፊው መሠራት እንዳለባቸው አመላካች ሆኗል፡፡

የድጋፍና እንክብካቤ ኘሮጀክት አተገባበርም ቢሆን ህብረተሰብ አቀፍና ዘላቂ መፍትሄ ላይ የተመረኮዘ ባለመሆኑ ገንዘብና ቁሣቁስ ከማከፋፈል ያለፈ ተግባር አይታይም፡፡ እስካሁን ድረስ ይህን ችግር ሊቀርፍ የሚችል በድጋፍና እንክብካቤ አፈፃፀም ዙሪያ የወጣ መመሪያ አለመኖሩ ከምክንያቶቹ አንዱ ሲሆን አሁን ያለው ገንዘብና ቁሳቁስን የማከፋፈል ሥራ የጥገኝነትን ሥሜት በማሣደግ የተወሳሰበ ችግር ውስጥ ሊያስገባን እንደሚችል በመሠጋቱ ከዚህ ችግር በአፋጣኝ መላቀቅ ይኖርብናል፡፡

ሌላው የቅንጅት /Networking/ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን የሚመለከት መመሪያ ባለመኖሩ ምክንያት ኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ቅንጅታዊ አሠራር እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ በተመሳሳይ ሥራ ላይ በመጠመድ ሳቢያ የሀብትና የጊዜ ብክነት እንዳይገጥመን መንቃት ይገባናል፡፡

የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች በወቅቱ አለመቅረባቸው አንዱ የታየ ችግር ነው፡፡ በየደረጃው ያሉ የሴክሬታሪያት አስተባባሪዎች በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተፈፀሙ ተግባራትን በንቃት በመከታተል ተሟልተውና ወቅቱን ጠብቀው እንዲደርሱ በማድረግ በኩል የሚቀራቸው መሆኑንና ይህም በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚደረጉ ጥረቶች ምን ያህል እንደሆነ ለመለካት እንቅፋት ሆኖ ይገኛል፡፡

የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች /VCT/ በየአካባቢው አለመኖራቸውና የምክር ሰጭውም ቁጥር አናሣ መሆን፣ ያሉትም ቢሆኑ የተሟላ የመመርመሪያ ኬሚካል አቅርቦት አለማግኘታቸው የVCT አገልግሎቱን ያገኙና የምርመራ ውጤታቸው ፖዘቲቭ የሆኑት ሰዎች ደግሞ ተከታታይነት ያለው የስነልቦና ድጋፍ የሚያገኙበት ሪፈራል ሲስተም ያለመዘርጋቱና የመረጃ ልውውጡ እጅግ የደበዘዘ በመሆኑ፣ እንዲሁም በቤት ውስጥ እንክብካቤና ድጋፍ ለመታገዝ ባለመቻሉ ችግሩን አባብሶታል፡፡

## 2.4 በክልሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭትን የሚያባብሱ ሁኔታዎች

በአማራ ክልል ለወረርሽኙ መስፋፋት ምክንያቶች በሕብረተሰቡ ዘንድ የባህሪ ለውጥ አለመታየቱ ነው፡፡ ለዚህም በክልሉ የሚታዩ ጉልህ ችግሮች አሉ በዋናነት፣

- የቅድመ ጋብቻ ወሲብና ከጋብቻ በኋላ በአንድ ያለመወሰን ልማድ መስፋፋቱ
- በዝቅተኛ የኢኮኖሚ አቅም ምክንያት የጤናው ሽፋን ውስን በመሆኑና የጤና ትምህርት የባህሪ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ በስፋት ለመስጠት አለመቻሉ፣
- የፆታ እኩልነትን ያላረጋገጠ ባህል በተለይ በገጠር የሚኖሩ ሴቶች ወደከተማ እንዲሰደዱና በዝሙት አዳሪነት እንዲሠማሩ ያደረገ መሆኑ፣
- በሕብረተሰቡ ዘንድ ሰፍኖ የኖረው የድብቅነት ባህሪይ በቤተሰብ ውስጥ የሥነ-ተዋልዶ ጤና ውይይትን በግልጽ ማካሄድ አለመቻልና በሕብረተሰቡ ውስጥ የኤድስን በሽታ ከሌላው በሽታ በተለየ በሃጥያት የመጣ አድርጎ በመገመት ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን በተለየ ዓይን በመመልከት ማግለልና አድልዎ መፈፀም፣
- ይህንንም ለመከላከል ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች/ወላጅ አልባ ሕፃናትን የተመለከተ ሕግ አለመረቀቁ፣
- ወሲባዊ ፍላጎትን የሚያባብሱ ልማዶች እየዳበሩ መምጣታቸው፣ ለምሳሌ የህገወጥ ቪዲዮ ቤቶች መስፋፋት፣ ጫትና የአልኮል መሸጫ ቤቶች መስፋፋት፣ ጎጂ ባህላዊ ልምዶችን ለማስወገድ የሚደረገው ጥረት አናሳ መሆን፣
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመቀነስ የቅንጅታዊ ጥረት አናሣ መሆኑ፣ በዚህ ዙሪያ የተሠማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቁጥር አናሣ መሆንና ያሉትም ቢሆኑ የባህሪ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ ያለመንቀሳቀሳቸውና በዘላቂ የመፍትሄ አቅጣጫ በተለይ ህብረተሰብ አቀፍ እርምጃ ላይ አለማተኮር፡፡
- በአመራር ላይ ያሉ አካላትም የመሪነት ሚናቸውን በአግባቡ መጫወት አለመቻላቸው፣
- ወጣቱም በፍላጎቱ ተደራጅቶ ለሚያደርገው ጥረት በቂ ድጋፍ መስጠት አለመቻልና የፖሊሲ ረቂቅ አለመኖሩ ቀደም ብሎ ተከስተው የነበሩ ችግሮች ናቸው፡፡

## 3. የተግባርና ኃላፊነት ትንተና /Mandate Analysis/

- በምክር ቤቱ ውሣኔዎችና የሥራ ኘሮግራሞች ላይ በመመሥረት የኤድስ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ የሚደረጉትን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ለተግባራዊነታቸውም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ የጠቅላላ ጉባኤው አባላት፣ መንግስታዊ ድርጅቶች፣ ግለሰቦችና ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ በመካከላቸው የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ በቅርብ ይከታተላል፣
- የክልሉ ኅብረተሰብ ስለ ኤድስ እና ችግሮቹ ግንዛቤ እንዲኖረው ክልላዊና አገር አቀፍ ስብሰባዎችና ዓውደ ጥናቶችን ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
- በክልሉ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ገጽታ ላይ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ እንደአስፈላጊነቱም ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያስተላልፋል፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የዞንና የወረዳ ቅርንጫፍ ሴክሬታሪያት ተወካዮችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣
- የአጭር የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የሥራ እዕቅድና በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ በእርሱም አማካኝነት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፣ ሲፀደቅም በአግባቡ በተግባር ላይ ያውላል፣
- የጠቅላላ ጉባኤውንና የሥራ አመራር ቦርዱን ውሣኔዎች ለክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት ያስተላልፋል፣ በወቅቱ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣
- ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል
- የሥራ እንቅስቃሴውን በተመለከተ ለቦርዱ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል፣ በየግማሽ አመቱ ደግሞ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፣
- ለጥናትና ምርምር ሥራዎች ድጋፍ ይሰጣል ያበረታታል፣

በአዋጁ የሚታዩ ክፍተቶች ነገር ግን ሊሠሩ የሚችሉ ተግባራት

- በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆጣጠር ሥራ ላይ ለመሥራት ወደክልላችን የሚመጡ መያድ ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ጋር የሥራ ስምምነት ሲያደርጉ ሴክሬታሪያቱ እንደ አንድ ተፈራራሚ አካል መወከል፣ የቴክኒክ እገዛ ማድረግና አፈፃፀሙን መከታተል፣
- ከብሔራዊ የኤች አይ ቪ/አድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣ ብሔራዊ ደረጃ የሚወጡ የሥራ መመሪያዎችን ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ሥራ ላይ ማዋል፣

## 4. የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/ሴክሬታሪያት ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች

### 4.1. ራዕይ /Vision

በአማራ ብሔራዊ ክልል የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ የሚያስከትለው ሰብዓዊ እልቂት፣ ኢኮኖሚያዊ ድቀት፣ ማህበራዊ ቀውስ እና የሥነ ልቦና ጉዳት ተወግዶ ማየት፣

### 4.2. ተልዕኮ /Mission

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ወረርሽኝ በክልሉ እንዳይስፋፋ ኅብረተሰብ አቀፍ፣ ዘላቂነት ያለው፣ የመከላከል እና የመቆጣጠር እንቅስቃሴዎችን በተቀናጀና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማካሄድ እንዲቻል የመ/ቤቶች፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የኅብረተሰብ አቀፍ ተቋማት /የወጣቶች ፀረ ኤድስ ክበባትና ማኅበራት፣ እድሮች፣ የሴቶችና ወጣቶች ማኅበራት/ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሠቦች የሚያደርጉትን ጥረት በመደገፍና በማስተባበር ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና በቫይረሱ ምክንያት ቤተሰቦቻቸውን ያጡ ሕፃናት ቀጣይነት ያለውና ራስን የሚያስችል ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ የአካባቢን ሀብት በዋነኛነት መሠረት የሚያደርግ ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ ማፈላለና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል፣

### 4.3. የአሠራር መርሆዎችና እሴቶች /Values

1. በትልቁ እናስባለን፣ በትንሹ አሁኑኑ እንጀምራለን!
2. ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችንና ወላጅ አልባ ሕፃናትን ሰብአዊ መብቶቻቸውን እናከብራለን! አድልዎና መገለል አናደርግም!
3. ሥራችንን ለማከናወን መደበኛ የሥራ ሰዓት አይገድበንም!
4. ከአጋሮቻችን ጋር በታማኝነት፣ በእኩልነትና፣ በፍትሃዊነት እንሰራለን!
5. በትምህርትም ይሁን በልምድ ያገኘነውን እውቀት ሥራችንን ለመፈፀም ተገቢ በሆነ መንገድ ሁሉ በተግባር ላይ እናውላለን!
6. የመ/ቤታችንን ቁሳዊና ሰብአዊ ሃብት በአግባቡ እንጠቀማለን!
7. ከተለያዩ ምንጮች የምናገኘውን የገንዘብ ሀብት በውጤታማ ሥራ ላይ እናውላለን!

## 5. ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ትንተና

| ተቁ | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ስም | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ከሴክሬታሪያቱ የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ሁኔታ | መ/ቤቱ በሴክሬታሪያቱ ያለው የተፈላጊነት ደረጃ | የሴክሬታሪያቱ ምላሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመንግሥት አካላት (GO) | ➢ የገንዘብና የሙያ ድጋፍ ማድረግና በሚቀርበው ኘሮጀክት መሠረት የሚጠየቀውን ድጋፍ በወቅቱ ማግኘት፣<br>➢ ግንዛቤ ማስጨበጥ የሚችሉ የማስተማሪያ ቁሣቁሶች በበቂ ሁኔታ መገኘትና ወቅታዊ መረጃዎች መለዋወጥ<br>➢ ቅንጅታዊ አሠራርን ማስፈን<br>➢ የሥራ ተግባር ዝርዝርና መመሪያ<br>➢ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች<br>➢ በሚዘጋጁ የማስተማሪያ ጽሁፎች ላይ አስተያየት ማግኘት | ➢ በህመምና በሞት ምክንያት በሠራተኛው ላይ የኢኮ ኖሚ፣ የማኅበራዊና ስነ-ልቦናዊ ቀውስ ይፈጠራል<br>➢ የበሽታው ስርጭት ይጨምራል ብዙ የመንግሥት ሰራተኞች አምራች ዜጎች ይሞታሉ፣<br>➢ የሴክተሩ ምርትና ምርታማነት ይቀንሳል<br>➢ በሰራተኛውና በተገልጋዩ ሕብረተሰብ የባሕሪ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት ይገታል፡፡<br>➢ የመረጃ ክፍተት ይፈጠራል | Primary | ➢ ግልጽ ራዕይ ይዞና በብቁ ባለሙያ ተደራጅቶ በሽታውን መከላከል<br>➢ የማስተባበር አቅምን በማጎልበት መንቀሳቀስ<br>➢ የገንዘብ ድጋፍ ከማድረግ ባሻገር በሁሉም የመንግሥት መ/ቤቶች ፎካል ፐርሰን መኖሩን ማረጋገጥና የሚሰሩ ሥራዎችን መከታተል፣<br>➢ በተለያዩ ድርጅቶች የሚታየውን የሥራ ድግግሞሽ ለማስወገድ ቅንጅታዊ አሠራርን መዘርጋት፣<br>➢ ድርጅቶቹ የሚጠበቅባቸውን ማድረግ እንዲችሉ የመፈፀም አቅማቸውን ማጎልበት<br>➢ በተለያዩ መ/ቤቶች ያሉ ኃላፊዎች በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ትኩረት ሰጥተው የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ መፍጠር<br>➢ የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ በተቀላጠፈ ሁኔታ የሚለቀቅበትን ስልት መንደፍ<br>➢ በኤች አይ ቪ/አድስ ዙሪያ ያሉና የሚወጡ ፖሊሲዎች ደንቦችና መመሪያዎች ማስተዋወቅና ማስረጽ |

| ተቁ | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ስም | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ከሴክሬታሪያቱ የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ሁኔታ | መ/ቤቱ በሴክሬታሪያቱ ያለው የተፈላጊነት ደረጃ | የሴክሬታሪያቱ ምላሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት/ዕድር፣ክበባት/ ማህበራትና/ የሀይማኖት ተቋማት | ➢ የገንዘብ የሙያና የማስተማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ<br>➢ ተከታታይ የሆነ ጉብኝት<br>➢ ሥልጠናዎችን በመስጠት አቅሙ እንዲጎለብት ማድረግ<br>➢ በእነርሱ ደረጃ ለሚሰሩ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሥራዎች የተግባር ዝርዝር መመሪያ | ➢ ለሕብረተሰቡ ተከታታይነትና ወጥነት ያለው ትምህርት ለመስጠት አቅሙ ያንሠዋል<br>➢ የኤች አይ ቪ/ሥርጭት ይጨምራል<br>➢ የተቋቋሙ ማህበራት ክበባት ይዳከማሉ፣ ሌሎችም አዳዲስ እንዳይፈጠሩ ያደርጋል፡፡ ኤች አይ ቪ/ኤድስን አካቶ የመሥራት ፍላጎት ይቀንሣል<br>➢ የሕብረተሰቡ ተሣትፎ በመቀነሱ በሽታውን ለመከላከል የሚያስችል ዘላቂ መሠረት መሆኑ ይቀራል<br>➢ መገለልና አድልዎ ይጨም ራል፣ የረዳት አልባ ሕፃናት ቀጥር ይበረክታል፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች ቁጥር ይጨምራል የወጣት አጥፊነት ባሕሪይ ይስፋፋል፡፡ | **Primary** | ➢ የአፈፃፀም ሁኔታን በመገምገም ውጤታማ እንቅስቃሴ የሚያደር ጉትን በመለየት የበለጠ ማበረታታት<br>➢ ለሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎች የተቀላጠፈ ምላሽ የሚሠጥ ሲስተም መዘርጋት<br>➢ ግልጽ የሆነ አሠራር በመዘርጋት፣ የሴክሬታሪያቱ ተግባርና ኃላፊነት በማህበረሰቡ እንዲታወቅ ማድረግ<br>➢ ማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት በገጠ ሩ አካባቢ የበለጠ እንዲደራጁ ትኩረት መስጠት<br>➢ በማህበረሰብ ደረጃ የተረጅነትን ስሜት የሚከላከል የአካባቢ ሀብትን መሠረት ያደረገ እንቅስቃሴ ማድረግ<br>➢ የሚሰጠው ድጋፍና እንክብካቤ የጥገኝነት ስሜትን የማይፈጥርና ዘለቄታዊ የሆነ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ሥልጠና ማዘጋጀት<br>➢ መመሪያ ማዘጋጀትና መስጠት |

| ተቁ | ጉዳዩ የሚመለ ከተው አካል ስም | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ከሴክሬታሪያቱ የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ሁኔታ | መ/ቤቱ በሴክሬታሪያቱ ያለው የተፈላጊነት ደረጃ | የሴክሬታሪያቱ ምላሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | NGOs /መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/ | ➢ የገንዘብና የማስተማሪያ ቁሣቁስ ድጋፍ<br>➢ የተጠናቀረ መረጃ ማግኘት<br>➢ በተለያዩ ሥልጠናዎች አቅም መገንባት<br>➢ የሥልጠና ማኑዋል ማግኘት<br>➢ የሚቀርቡ ኘሮጀክቶችን በፍጥነት ገምግሞ ምላሽ መስጠት<br>➢ የተግባር ዝርዝር መመሪያ ማዘጋጀት | ➢ ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላ ቸው ወላጅ አልባ ሕፃናት ለጎዳና ሕይወት ይጋለጣሉ፣<br>➢ በድርጅቶቹ የሚደረገው ጥረት ይዳከማል፣<br>➢ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ለመንቀሣቀስ የሚፈልጉ ሀገር በቀል ድርጅቶች አይፈጠሩም<br>➢ የበሽታው ስርጭት የከፋ ይሆናል<br>➢ የበሽታውን ሥርጭት ለመግ ታት የመንግስት እንቅስቃሴ ብቻ የመሆን አዝማሚያ ያመጣል | **Primary** | ➢ ለሚጠየቀው ድጋፍ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት የሚችል መዋቅር መዘርጋት<br>➢ የኘሮጀክት ግምገማና ማጽደቅ የተቀላጠፈ ለማድረግ የአሠራር ሲስተም መዘርጋት<br>➢ የክትትልና የግምገማ ሥርዓትን መዘርጋት<br>➢ ቀንጅታዊ የአሠራር ሲስተም መፍጠር<br>➢ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ማዘጋጀት<br>➢ ኤች አይ ቪ/ኤድስን አካቶ የመስራት/mainstreaming guideline/ ማዘጋጀት<br>➢ ፍትሃዊነትን የተላበሰ ያልተንዛዛ ግልፀኝነት ያለው አሠራር ማስፈን፣<br>➢ ዎርክሾፖችንና አውደ ጥናቶችን ማዘጋጀት<br>➢ በተወሰነ ጊዜ የምክክር ፎረም ማዘጋጀት |

| ተቁ | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ስም | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ከሴክሬታሪያቱ የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ሁኔታ | መ/ቤቱ በሴክሬታሪያቱ ያለው የተፈላጊነት ደረጃ | የሴክሬታሪያቱ ምላሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና የወላጅ አልባ ሕፃናት ማህበራት /PLHAS/ORPHANS **Associations/** | ➢ የበጀት የቴክኒክና የቁሣቁስ ድጋፍ<br>➢ የተለያዩ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት አቅሙ እንዲጎለብት<br>➢ ለሚቀርቡ የኘሮጀክት ኘሮፖዛሎች አፋጣኝ ምላሽ ማግኘት<br>➢ የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር<br>➢ ተከታታይነት ያለው ጉብኝትና ትኩረትን መሻት<br>➢ የአሠራር መመሪያዎችና ደንቦችን መጠበቅ | ➢ በማህበር የሚታቀፉ አባላት በቂ ድጋፍ ባለማግኘታቸው በማህበር የመቆየት ፍላጎታ ቸው ይዳከማል፣<br>➢ በማህበሩ የሚደገፉ አባላት በቂ ድጋፍ ካለማግኘት ለስቃይና ለእንግልት ይዳረጋሉ<br>➢ አባላትን በብዛት ለማቀፍ ማህበሩ አቅም አይኖረውም፣<br>➢ ማህበሩ የመፍረስ አደጋ ያጋጥመዋል<br>➢ ማህበሩ የሚያደርገው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ይዳከማል<br>➢ መገለልና መድሎ ይበረታል በዚህም ምክንያት የበሽረው ሥርጭትና የሞት መጠን ይጨምራል፡፡<br>➢ በዝምታው መጠናከር የተነሳ በሽታው ምስጢር ሆኖ ሰብአናዋ ጥፋቱን ይቀጥላል፡፡ | **Primary** | ➢ ለሚቀርቡ የበጀትና የቁሣቁስ ድጋፍ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ ሲስተም መዘርጋት<br>➢ የተሻለ ቅንጅታዊ የአሠራር ሲስተም መዘርጋት<br>➢ የሪፈራል ሲስተም እንዲኖር ማድረግ፣<br>➢ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያደርጉ ድርጅቶችን ማበረታትና መደገፍ<br>➢ የሥልጠና ኘሮግራሞችን ማዘጋጀት፣<br>➢ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ አባላት ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበርና እነርሱም የሌላውን እንዲያከብሩ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር ማድረግ፣<br>➢ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና ወላጅ አልባ ሕፃናት በዘላቂነት ራሳቸውን የሚደግፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት<br>➢ የእድሜ ማራዘሚያ መድሃኒት የሚገኝበትን initiative/ስልት ማበረታታትና፣ መቀየስ |

| ተቁ | ጉዳዩ የሚመለ ከተው አካል ስም | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ከሴክሬታሪያቱ የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ሁኔታ | መ/ቤቱ በሴክሬታሪያቱ ያለው የተፈላጊነት ደረጃ | የሴክሬታሪያቱ ምላሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የግል ድርጅቶች /POS/ | ➢ የገንዘብና የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ድጋፍ<br>➢ የሥልጠና ድጋፍ<br>➢ የVCTአገልግሎት ትኩረት እንዲያገኝ<br>➢ የVCT guideline እንዲዘጋጅ/እንዲሰራጭ<br>➢ የመረጃ ልውውጥ እንዲጠናከር<br>➢ ለሚቀርቡት የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች አፋጣኝ ምላሽ ማግኘት | ➢ የVCT አገልግሎቶች አይስፋፉም<br>➢ በግል ክሊኒኮች የሚካሄደውና Opportunistic በሽታዎች የሚደረገው የሕክምና አገልግ ለት ይዳከማል<br>➢ የበሽታው ሥርጭት ይስፋፋል<br>➢ በኤድስ ዙሪያ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ይዳከማል | **Primary** | ➢ ለሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጥ ሲስተም መዘርጋት<br>➢ ቅንጅታዊ የአሠራር ሲስተም መዘርጋት<br>➢ የመረጃ ልውውጥ ሥርአት መዘርጋት<br>➢ መመሪያዎችና ደንቦችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት<br>➢ የVCT አገልግሎት እንዲሰጡ ማበረታታት<br>➢ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ማበረታታት |
| 6 | ለጋሽ ድርጅቶች /DONORS & UN Agencies/ | ➢ ወቅታዊ የእቅድ ዝግጅት እንዲኖር ይጠብቃሉ<br>➢ የሚያወጡትን ደንብና የሥራ መመሪያዎችን እንድንከተል ይፈልጋል<br>➢ የሚሰጡንን የማቴሪያልና የገንዘብ ድጋፍ ለታቀደለት አላማ ማዋልን<br>➢ የተፋጠነና ግልፀኝነት ያለው አሠራርና የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ስልት እንዲኖረን ይጠብቃሉ<br>➢ ሪፖርት በወቅቱ እንዲደርሳቸው ይጠ ብቃሉ | ➢ የሚያደርጉትን ድጋፍ ያቆማሉ<br>➢ የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚደረገው ርብርብ ይዳከማል፣<br>➢ የበሽታው ስርጭትና የሚያስከ ትለው ጉዳት ይጨምራል<br>➢ በሌሎች የልማት ዘርፎች የሚደረግ እንቅስቃሴ ይዳከማል | **Primary** | ➢ ወቅታዊ የእቅድ ዝግጅትና ሪፖርት የሚቀርብበትን ስልት መቀየስ<br>➢ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ<br>➢ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ የእርዳታ ድርጅቶችን ደንብና መመሪያ መከተል<br>➢ የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋትና በተወሰነ ወቅት ውይይት የሚካሄድበትን ፎረም ማዘጋጀት<br>➢ ግልፀኝነት ያለውና ያልተንዛዛ አሠራርን መከተል |

| ተቁ | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ስም | ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ከሴክሬታሪያቱ የሚጠብቀው | የሚጠበቀው ካልተሟላ ሊከሰት የሚችለው ሁኔታ | መ/ቤቱ በሴክሬታሪያቱ ያለው የተፈላጊነት ደረጃ | የሴክሬታሪያቱ ምላሽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የክልሉ መንግሥት /Regional state/ | ➢ በአዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በተገቢው መንገድ እንዲወጣ ይጠብቃል<br>➢ ወቅታዊ የእቅድ ዝግጅትና የአፈፃፀም ሪፖርት<br>➢ መደበኛ ጉባዔና ስብሰባዎች ወቅታቸውን ጠብቀው ማካሄድ<br>➢ የክልሉ የኤድስ መከ/ጉባኤ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት መንቀሳቀስ<br>➢ ከተለያዩ ምንጮች ሀብት በማፈላለግ የተገኘውን በአግባቡና በፍትሃዊነት ሥራ ላይ እንዲውል<br>➢ የክልሉን ሕግና ደንብ የተከተለ አሠራርና የተጠናከረ ክትትልና ግምገማ እንዲኖር | ➢ የአመራርና የአደረጃጀት ለውጥ ያደርጋል<br>➢ መንግሥት የሚያደርገውን የድጋፍ በጀት ይቀንሳል | **Primary** | ➢ በአዋጅ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ለመፈፀም የሚያስፈልገውን አደረጃጀት መዘርጋት<br>➢ ወቅታዊ የእቅድ ዝግጅትና የሪፖርት ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ<br>➢ ወቅታቸውን የጠበቁ ጉባዔዎችና ስብሰባዎችን ማካሄድ<br>➢ የክልሉ የኤድስ መከ/መቆ/ጉባዔ በሚሰጠው አቅጣጫ መሄድ<br>➢ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት ማስፈን<br>➢ የክልሉን ሕግና ደንብ የተከተለ ያልተንዛዛ አሠራርን መከተልና የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት፣ |

# 6. የሁኔታዎች ትንተና

## 6.1 የውጫዊ ሁኔታዎች ትንተና

| ተቁ | ውጫዊ ሁኔታ | ምቹ ሁኔታ | ሥጋት |
|---|---|---|---|
| 1 | ፖለቲካዊ<br>- የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፖለሲ መኖር | ➢ ቫይረሱን ለመከላከል የሚደረገው ጥረት የሁሉንም ትኩረት እንዲያገኝ ይረዳል<br>➢ ቫይረሱን በአደረጃጀት ለመከላከል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ | |
| | - የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ | ➢ የሴቶችን በማንኛውም እንቅስቃሴ በእኩልነት መሳተፍ ስለሚደነግግ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ በሚቀረፀው ፕሮጀክቶች ሴቶች ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። | |
| | - የኤድስ መከ/መቆ/ ምክር ቤት መቋቋም | ➢ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ተግባር ፖለቲካዊ ትኩረት እንዲያገኝ ይረዳል፣ | |
| | -የኤድስ መከ/መቆ/መዋቅር እስከ ቀበሌ መዘርጋቱ | ➢ ኅብረተሰቡን በቅርበት በማስተባበር የበሽታውን ስርጭት በዘላቂነት ለመግታት እድል ይሠጣል፣ | ➢ የሰለጠነና ብቁ የሠው ኃይል ለማሟላት ያስቸግራል |
| | - የሥራ አመራር ቦርድ መቋቋም | ➢ ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር የዕለት ከዕለት ሥራ በቅርብ አመራር በመስጠት ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ያግዛል፣ | ➢ አባላቱ በሌሎች ወቅታዊ ሥራዎች የሚጠመዱ በመሆኑ መደበኛ ስብሰባዎ ችን ለማካሄድና ውሳኔ ለማሳለፍ ያስቸግራል |
| | - የሪቪው ቦርድ መቋቋም | ➢ ሙያዊ ስብጥርን በመፍጠር ፕሮጀክቶች ከተለያዩ ማዕዘናት እንዲታዩ ያደርጋል፣ | ➢ ፕሮጀክቶች በተፈለገው ፍጥነትና መጠን አይታዩም፣<br>➢ አባላቱ ከሴክሬታሪያቱ ውጪ በመሆናቸው እንደ ተፈለገ ያለመገኘትና አሰባስቦ ለማሠራት አይቻልም |
| | - የጤና ፖሊሲ | ➢ በመከላከል ላይ ያተኮረ በመሆኑ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያግዛል | |
| | - የሀገሪቱ የውጪ ፖሊሲ | ➢ በርካታ ረጅ ድርጅቶችና መንግስታት ወደ ሀገራችን ገብተው ኤች አይ ቪ/ኤድስን ፕሮግራም እንዲደግፉ አድርጓል | |
| | - የወጣቶች ፖሊሲ | ➢ ወጣቶች በአካባቢያቸው ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ ስለሚፈቅድ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆ/ ይረዳል | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | **<u>ኢኮኖሚያዊ</u>**<br>- የነፃ ገበያ ፖሊሲ | ➢ የግል ድርጅቶችም በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና/መቆጣጠር ላይ እንዲሳተፉ እድል ስለሚሰጥ ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ያግዛል | |
| | -የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ | ➢ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መስፋፋት ድህነት አንዱ መንስኤ በመሆኑ ድህነትን ለመቀ ነስ በሚደረገው ጥረት ኤች አይ ቪ/ኤ ድስን ለመከላከል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል | |
| | - ለጋሽ ድርጅቶች /አለምአቀፍ/ | ➢ የኤች አይ ቪ/ኤድስን መከ/መቆ/ ኘሮግራ ሞችን ለመደገፍ ተነሳሽነት ማሳየታቸው<br>➢ ለሀገሪቱ ብድር ሲፈቀድ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ እንደአንድ ኮምፖነንት መካተቱን ማረጋገጥ | ➢ ከፍተኛ የሆነ የጥገኝነት ስሜት እንዲዳብር ያደርጋል<br>➢ መንግስትን በሀገሪቱ አቅም እንዳይንቀሳቀስ ያደርገዋል፡፡ |
| | - መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/መያድ/ | ➢ በሽታውን በመከላከልና መቆጣጠር ረገድ ያለብንን ክፍተት/በሰው ኃይልም ይሁን በገንዘብ/ በመሙላት ያግዛሉ፡፡ | ➢ የባህል መሸርሸር ያጋጥማል<br>➢ የተረጂነት ስሜት ይጨምራል<br>➢ በከተማ ላይ በቻ የማተ ኮርና ገጠሩን የመርሳት ችግር ያጋጥማል |
| 3 | **<u>ማህበራዊ</u>**<br>- የቤተሰብና<br>ጋብቻ ህግ | ➢ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ እንዲመሠረት ስለሚጠይቅ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል ያግዛል<br>➢ በኤች አይ ቪ/ኤድስ በተለይ ተጎጂ የሆኑትን ሴቶች ለመርዳት ልዩ ድጋፍ እንዲደረግ ስለሚፈቅድ ያግዛል | ➢ የቅድመ ጋብቻ የደም ምርመራ ባለመኖሩ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭት ከቁጥጥር ውጪ የመሆን እድል አለው፡፡ |
| | -የህፃናት መብት ድንጋጌዎች | ➢ የህፃናት መብት እንዲከበርና ቅድሚያ ትኩረት እንዲያገኝ መደረጉ ለወላጅ አልባ ሕፃናት እንክብካቤና ድጋፍ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡<br>➢ ወላጅ አልባ ህፃናት በማህበረሰቡ ድጋፍ እን ዲያድጉ ስለሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ነው | ➢ የህፃናት መብቶች በባህላዊም ሆነ በኅብረተሰቡ ያለመታወቁና ቀዳሚ ትኩረት ያለማግኘቱ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚ ለማድረግ ያለመቻሉ፡፡ |
| | - የህብረተሰቡ እይታ | ➢ ሴክሬታሪያቱ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል የተቋቋመ መሆኑን ኅብረተሰቡ ማወቁ ለሥራችን አፈፃፀም እገዛ ያደርጋል | ➢ ኅብረተሰቡ የኤች አይ ቪ/ኤድስን ሥራ ለሴክሬ ታሪያቱ ብቻ የተተወ አድርጎ መመልከቱ ዘርፈ ብዙውን እንቅስቃሴ የሚገታውና ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርግ ያደርጋል<br>➢ የበጀት አጠቃቀማቸው ደካማ ነው የሚል እይታ/25%/ ብቻ<br>➢ ለሚቀርቡ ኘሮጀክቶች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት አይችሉም መባሉ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ➢ ወርክሾፕና አውደጥናት ያበዛሉ የሚል ዕይታ ፈጥሯል፡፡ |
| 4 | የቴክኖሎጂ ሁኔታዎች | ➢ የኮምፒውተር፣የፋክስ፣ስልክና የኢንተርኔት አገ/ሥራ ላይ መዋል መረጃን በቀላሉ ለማግኘትም ሆነ ለማሰራጨት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡<br>➢ የትራንስፖርትና የፖስታ አገ/መዘርጋቱ | ➢ አገልግሎቱ በወረዳዎች ባለመዳረሱ ምክንያት መያ ዶች በወረዳዎች ገብተው በኤድስ ዙሪያ እንዳይንቀሳቀሱ እንቅፋት ፈጥሯል፡፡<br>➢ የአገ/ክፍያው ውድ በመሆኑ ምክንያት ለሁሉም መረጃን በቀላሉ ለማስተላለፍ አይቻልም፡፡<br>➢ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎቹ በራሳቸው ውድ በመሆና ቸው ተጠቃሚዎችን ማበራ ከት አለመቻሉ፡፡ |

## 6.2 የውስጣዊ ሁኔታ ትንተና

| ተቁ | ውስጣዊ ሁኔታ | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|---|
| 1 | የሰው ኃይል | ➢ የሙያ ስብጥር መኖር<br>➢ የሠለጠነና ብቃት ያለው መሆን<br>➢ በቡድን/በቅንጅት መሥራት መቻል | ➢ በቂ የሰው ኃይል ያለመኖሩ<br>➢ በሥራው ላይ የሚያስፈልጉ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎችን አለማግኘቱ<br>➢ የሰው ኃይል ስብጥሩ ፆታን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑ<br>➢ በታችኛው ደረጃ /ወረዳ/ያሉ ሠራተኞች በስራ ላይ ተረጋግቶ ያለመቆየት አዝማሚያ መታየቱ<br>➢ በጽ/ቤቱ ውስጥ ያለው የድጋፍ አሠጣጥ የተሟላ አለመሆን፡፡ |
| 2 | ቁሳዊ ሁኔታ | ➢ የቢሮና የቢሮ እቃዎች የተሟሉ መሆናቸው<br>➢ የኦዶቪዥዋል መሣሪያዎች የተሟሉ መሆናቸው | ➢ የተሽከርካሪዎች /ሞተርን ጨምሮ/ እጥረት መኖሩ |
| 3 | የፋይናንስ ሁኔታ | ➢ ምንጩ የተለያየ መሆኑ በሥራ ላይ እንደሁኔታው መጠቀም አስችሏል<br>➢ የፋይናንስ ሥርዓቱና አለቃቀቁ ግልጽና ቀልጣፋ መሆኑ | ➢ ወጥ የሆነ አሠራር አለመኖሩ<br>➢ በወረዳ ደረጃ ካለው የፋይናንስ ስርዓት ጋር የተጣጣመና በሥልጠና የተደገፈ እውቀት የሌላቸው ሠራተ ኞች መሆናቸው |
| 4 | የሠራተኛው እይታ | ➢ | ➢ ልዩ ልዩ የሠራተኛው ጥቅሞች ባለመከበራቸው ስለድርጅቱ ዘላቂነት በጎ እይታ የለም<br>➢ አስተማማኝ የሥራ ዋስትና ባለመኖሩ ለሠራተኛው ያለመረጋጋት ችግር ፈጥሯል፡፡ |
| 5 | አገልግሎቶች /Service/<br>➢ ሲስተም | ➢ ከላይኛው እስከታችኛው ደረጃ የግንኙነት ሠንሠለት መዘርጋቱ፡፡ | ➢ የግንኙነት ሠንሠለቱን ጠብቆ የሥራ ሪፖርት በወቅቱ አለመድረሱ<br>➢ የተጀመሩ ሥራዎች ያሉበትን ደረጃ ሁሉም ሠራተኛ በእኩል ሁኔታ ኢንፎርሜሽን የሌለው መሆኑ፡፡<br>➢ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛው በብዛት ስለወረርሽኙም ሆነ ስለጽ/ቤቱ እንቅስቃሴ ያለው እውቀት የጠለቀ አለመሆኑ፡፡ |
| | ➢ መዋቅር | ➢ ከአዲሱ አደረጃጀት ጋር የተጣጣመ መሆኑ<br>➢ የተለያዩ የሙያ ስብጥሮች በመዋቅሩ የተካተተ መሆኑ<br>➢ እስከታችኛው የአደረጃጀት ደረጃ/ቀበሌ/የደረሰ በመሆኑ ከሕዝብ ጋር የተገናኘ መሆኑ | ➢ ከአመት በላይ ለሆነ ጊዜ መዋቅሩን ለማጽደቅ ሳይታይ በመቆየቱ በሥራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡<br>➢ በፑል መካተቱ የድጋፍ ሰጪው ክፍል አሁን ካለው የአሠራር ፍጥነት ጋር ስለማይሄድ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከላከል ድንገተኛ/Emergency/ አሠራር የተጓተተ ያደርገዋል |

# 7. የስትራቴጂክ እቅድና ሥራ አመራር ግቦችና ዓላማዎች

## የአቅም ግንባታ /CAPACITY BUILDING/

1. **ግብ፤** በክልሉ ውስጥ በፕሮጀክት የሚታቀፉ ወረዳዎችን ማሳደግ

   **ዓላማዎች፤**

   1.1. በአትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የኤድስ መከ/መቆ/ፕሮግራም የታቀፉ 20 ወረዳዎችን ወደ 47 ከፍ ማድረግ

   1.2. በአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ የሚታቀፉ ወረዳዎችን ከ5 ወረዳዎች ወደ 11 ከፍ ማድረግ፣

   1.3. በሲዳ ፕሮግራም 16 ወረዳዎች እንዲታቀፉ ማድረግ

   1.4. በዩኤንዲፒ ፕሮግራም 16 ወረዳዎች እንዲታቀፉ ማድረግ

   1.5. በክልሉ በኤድስ ዙሪያ ለመሥራት በሚመጡ የተለያዩ ድርጅቶች 10 ወረዳዎች እንዲታቀፉ ማድረግ፣

2. **ግብ፤** የክልል የዞንና የወረዳ የኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤቶችን የማስፈፀም አቅም እንዲሻሻል ማድረግ፣

   **ዓላማዎች፤**

   2.1. በፕሮጀክት ዝግጅትና አመራር ሙያ 105 የወረዳ አስተባባሪዎችና 10 የዞን አስተባባሪዎችን ማሠልጠን፣

   2.2. 105 የወረዳ የሂሣብ ሠራተኞችን በዘመናዊ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ማሠልጠን

   2.3. 8 የክልል የኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ቤት ባለሙያዎችን በፕሮጀክት ዝግጅትና ሥራ አመራር ሙያ ማሠልጠን

3. **ግብ፤** የጽ/ቤቱን የፕሮጀክት ምዘናና ግምገማ ሥርዓት የተቀላጠፈ ማድረግ

   **ዓላማዎች፤**

   3.1. በአመት ይታይ የነበረውን 52 የፕሮጀክት ጥናቶች በየአመቱ ወደ 100 በማሳደግ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ

   3.2. ፕሮጀክት ከሚያቀርቡት ድርጅቶች ውስጥ በየአመቱ 50 ለሚሆኑት የፕሮጀክት ጥናትና አቀራረብ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣

4. **ግብ፤** የመንግስት ሴክተሮችንና ድርጅቶችን በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ያላቸውን እንቅስቃሴና ተሳትፎ ማሳደግ

   **ዓላማዎች፤**

   4.1. የተሳታፊ መንግስት ሴክተሮችን/ድርጅቶችን ቁጥር ከ20 ወደ 60 ማሳደግ

4.2. የኤች አይ ቪ/ኤድስ ተጠሪ ሙያተኞችን/focal person/ ቁጥር ከ18 ወደ 60 ከፍ እንዲል ማድረግ፣ /በሁሉም መንግሥት ሴክተሮች/ድርጅቶች/

4.3. 60 የኤች አይ ቪ ኤድስ ተጠሪዎች /focal persons/ የፕሮጀክት ዝግጅትና ሥራ አመራር ሥልጠና እንዲወስዱ ማድረግ

5. **ግብ፤** በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ዙሪያ የሕዝብ ተሳትፎን /የኅብረተሰቡን ተሳትፎ/ ማሳደግ

**ዓለማዎች፤**

5.1. በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የሚሠሩ አሁን ያሉትን 110 ክበባትንና ማህበራትን ማጠናከር

5.2. 55 የሚሆኑ አዳዲስ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የሚሠሩ ክበባትና ማህበራት እንዲመሠረቱ ማድረግ

5.3. በቀበሌ ደረጃ ቢያንስ አንድ ዕድር የኤች አይ ቪ/ኤድስን አካቶ እንዲሠራ መደገፍ

5.4. 660 የሚሆኑ የኅብረተሰብ አቀፍ ተቋማት ማኅበራትና/ክበባት የቤት ለቤት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በዘርፉ ማሠልጠን

6. **ግብ፤** የክልል የዞንና የወረዳ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤቶችን ማጠናከር

**ዓላማዎች፤**

6.1. 33 የወረዳ ጽ/ቤቶችን በቁሳቁስና የሰው ኃይል ማደራጀት

6.2. ለ45 የወረዳ ጽ/ቤቶች የሞተር ብስክሌት ግዢ ማከናወን

6.3. ለ11 የዞን የኤች የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/ጽ/ቤቶች የኮምፒውተር አገ/እንዲኖራቸው ማድረግ፣

6.4. የክልሉ ሴክሬታሪያት 2 አዲስ መኪናዎች እንዲኖሩት ማድረግ፣

# IEC/BCC

7 **ግብ፤** በኅብረተሰቡ ዘንድ የባሕሪይ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ

**ዓላማዎች፤**

7.1 የባህሪይ ለውጥ አምጪ የአሠልጣኞች ስልጠና የወሰዱ ባለሙያዎችን ቁጥር ከ39 ወደ 250 ማሳደግ፣

7.2 የመልዕክት አቀራረጽና የመረጃ ሥርፀት ስርዓት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ በማድረግ ጥራቱ አሁን ካለበት በ50% ማሻሻል፣

7.3 የመሪነት ሚና በየደረጃው የተሟላ እንዲሆን 339 /በወረዳ 3 ያህል/ መሪዎችን /ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካና ከአካባቢ ሕብረተሰብ/ ማፍራት፣

8. <u>ግብ፤</u> በክልሉ ውስጥ የኮንዶም ስርጭትንና አጠቃቀምን ማሻሻል

<u>ዓላማዎች፤</u>

8.1. በክልሉ ውስጥ የኮንዶም ተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ከ7% ወደ 12% ከፍ እንዲል ማድረግ

8.2 በክልሉ ውስጥ የኮንዶም አጠቃቀም ግንዛቤን በ50% ማሻሻል፣

9. <u>ግብ፤</u> የአባላዘር በሽታዎች ሕክምናና ቁጥጥር እንዲሻሻል ማድረግ

<u>ዓላማዎች፤</u>

9.1 በጤና ቢሮ የሚካሄዱትን የአባላዘር ሕክምናና ቁጥጥር የሚደግፍ ሥልጠና ለ169 ጤና ተቋሟት መስጠት

9.2 በክልሉ ውስጥ በጤና ቢሮ ስር የሚገኙ 169 የጤና ተቋማት የተጠናከረ የአባላዘር ህክምናና ቁጥጥር እንዲሰጡ መደገፍ

10. <u>ግብ፤</u> በክልሉ ውስጥ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት እንዲዳረስ ማድረግ፣

<u>ዓላማዎች፤</u>

10.1 በክልሉ ውስጥ የሚገኙት 100 ወረዳዎች የVCT አገልግሎት እንዲኖራቸው ማድረግ፣

10.2 የVCT አገልግሎት ለሚሠጡ 100 የምክር አገልግሎት ሰጪዎች የምክር አገልግሎት አሠጣጥ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ

10.3 የVCT አገልግሎት ለሚሰጡ 100 የላብራቶሪ ቴክኒሽያኖች ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣

10.4 በአንድ ቀበሌ ሶስት የሚሆኑ የሕብረተሰብ አቀፍ ተቋማት የምክር አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የምክር አገልግለት አሠጣጥ ሥልጠና መስጠት

11. <u>ግብ፤</u> የክልሉ ታካሚ ሕብረተሰብ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ የነፃ የደም አቅርቦት እንዲያገኙ ማድረግ

<u>ዓላማዎች፤</u>

11.1. የክልሉ 7 ሆስፒታሎች የተሻሻለና ከኤች አይ ቪ/ኤድስ የነፃ የደም አቅርቦት እንዲኖራቸው ድጋፍ ማድረግ፣

11.2 በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የቀይ መስቀል የደም ባንኮች ከኤች አይ ቪ/ኤድስ የነፃ የደም አቅርቦት እንዲኖራቸው መደገፍ፣

12. **ግብ፤** በክልሉ ውስጥ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ከእናት ወደ ህፃን የሚተላለፍበትን መጠን መቀነስ

**ዓላማዎች፤**

12.1 በክልሉ ውስጥ ቫይረሱ ከእናት ወደ ህፃን እንዳይተላለፍ መከላከያ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሆስፒታል ከአንድ ወደ 3 ከፍ ማድረግ፣

12.2 በክልሉ ውስጥ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ከእናት ወደ ህፃን እንዳይተላለፍ አገልግሎት የሚያገኙትን እናቶች ቁጥር በእጥፍ ማሳደግ፣

## ድጋፍና እንክብካቤ/Care & Support /

13. **ግብ፤** በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት ማስፋፋትና ማጠናከር

**ዓላማዎች፤**

13.1. የወላጅ አልባ ህፃናት/ ድጋፍና እንክብካቤ ሽፋንን በ20% ማሳደግ

13.2. አሁን ድጋፍ የሚያገኙ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ 2402 አባላትን ወደ 13000 ከፍ እንዲል ማድረግ፣

13.3. 3 የነበሩትን የቫይረሱ ጋር የሚኖሩ/ወላጅ አልባ ሕፃናት ማኅበራትን ቁጥር ወደ 11 ከፍ እንዲል ማድረግ፣

13.4. 20% የሚሆኑ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩና ወላጅ አልባ ህፃናትን በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ፣

## የሰብአዊ መብት ጥበቃ /Human Rights /

14. **ግብ፤** ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና ወላጅ አልባ ሕፃናት ሰብዓዊ መብት በተሟላ መንገድ እንዲከበር ማድረግ

**ዓላማዎች፤**

14.1 በኅብረተሰቡ ውስጥ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና ወላጅ አልባ ሕፃናት የሚደርስባቸውን መገለልና አድልዎ ለማስቀም የሚያስችል ተከታታይ ትምህርት መስጠት፣

14.2 ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ህፃናት የኅብረተሰቡን ሰብዓዊ መብት ተረድተው እንዲያከብሩ ለማስቻል ተከታታይነት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ፣

## ጥናትና ምርምር

15. **ግብ፤** በክልሉ ውስጥ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን ማጠናከር

**ዓላማዎች፤**

15.1 በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ በጥናትና ምርምር የሚሳተፉ ድርጅቶችና ግለሡቦች

እንዲበራከቱ ማድረግ፣

15.2 በክልል ደረጃ በኤች አይ ቪ/ኤድስ አንድ የመረጃ ማዕከል/database /እንዲቋቋም ማድረግ፣

15.3 በክልለ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤት የመረጃ ማዕከል አንድ የኢንተርኔት አገ/በመክፈት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ወቅታዊ መረጃ እንዲኖር ማድረግ፣

# 8. የቁልፍ ጉዳዮች ትንተና

## የተመረጡ ስትራቴጂክ ጉዳዮችና የተቀመጡ አማራጮች

1 ለሚቀርቡ የኘሮጀክቶች ኘሮፖዛሎች አፋጣኝና ቀልጣፋ ምላሽ መስጠት አለመቻል፡

ስትራቴጂክ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት፤

- በክልሉ ውስጥ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ስርጭትን በመግታት ረገድ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የኀብረተሰብ አቀፍና የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም የግል ድርጅቶች የሚያቀርቡት የኘሮጀክት ኘሮፖዛል ፍጥነት ባለው መልኩ መልስ ማግኘት አለመቻሉ የመከላከሉን ሥራ በመስተጓጎሉ፣
- ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ ኘሮጀክቶች በፍጥነት መታየት ባለመቻላቸውና ድጋፍ ባለማግኘታቸው ሊተገበሩ ያለመቻላቸው፣
- በተሻለ ርብርብ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ዘለቄታዊ ውጤት ለማምጣት ከታሰበ የሁሉም ርብርብ የግድ ስለሆነ ከተለያየ አቅጣጫ የሚቀርቡ ኘሮጀክቶችን ተቀብሎ ሥራ ላይ ማዋል ወሣኝነት ያለው በመሆኑ።

## በአማራጭ ካልተሄደ የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት

የሚቀርቡ ኘሮጀክቶች በአፋጣኝ እየታዩ ምላሽ የማያገኙ ከሆነ ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተሟላና ኀብረተሰቡን ባሳተፈ መንገድ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለማይቻል የበሽታው ስርጭት በከፋ ሁኔታ ይባባሳል። ይህ ደግሞ የኀብረተሰቡን ማኀበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ ጉዳት በማባባስና የባሰ ቀውስ ውስጥ በማስገባት ለባሰ ድህነትና ማቆሚያ ለሌለው አደጋ የተጋለጠ እንዲሆን ያደርጋል።

## የተወሰደ አማራጭ

ለኤድስ መከ/መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡ ኘሮጀክቶችን የመመዘንና ለውሳኔ የማቅረብ ሂደት በጽ/ቤቱ ባለሙያዎች በቅድሚያ ታይቶ እንዲያልቅ እንዲደረግና ለመጨረሻ ውሳኔ ብቻ ለሥራ አመራር ቦርድ እንዲቀርብ ቢደረግ በተሻለ ፍጥነት ምላሽ መስጠት ያስችላል።

2. <u>ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ሕፃናት ዘንድ የሚፈጠረውን የእርዳታ ጠባቂነት ስሜት መስበር ያለመቻል</u>

በሀገሪቱ ደረጃ በተንሠራፋው ድህነትና ድርቅ ሳቢያ ችግሩን ለመቅረፍ ወደሀገር ውስጥ ከገቡ የእርዳታ ድርጅቶች እርዳታ መቀበል የተለመደ በመሆኑ የሥራ /ሠርቶ የማደር/ መንፈስ እየተዳከመ መጥቷል፡፡ በዚህም የተነሳ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ የመጣውን ገንዘብ እንደ ዜግነት መብት የመቁጠርና የመጠየቅ አዝማሚያ ታይቷል፡፡ ይህ ደግሞ ትንሽም ብትሆን የአካባቢን ሀብት የመጠቀም አቅጣጫ እንዳይታይ እያደረገ ነው፡፡

- የተገኘን የእርዳታ ሀብት በጥሬ ገንዘብ የማዳረስ /የማደል/ ተግባር ለአፈፃፀም በጣም ቀላል በመሆኑ በበርካታ አካባቢዎች ወደዚህ አቅጣጫ የመሄድ አዝማሚያ በስፋት ይታያል፡፡
- ከዚህ ጋር ተያይዞ ለረጅም ጊዜ የፈጠራ ባህልን የማዳበር እንቅስቃሴ መዳከሙ የኅብረተሰቡን የተለያዩ አካላት የመጠበቅ መንፈስ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓል፡፡ ይህም ለራሳቸው በራሳቸው ለችግራቸው አካባቢያዊ መፍትሄ እንዳይፈለግ እያደረገ ይገኛል፡፡

<u>በሥራችን ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት</u>

ባለብን ድህነት ላይ የምናገኛትን አነስተኛ ብድርና እርዳታ በጥሬ ገንዘብ እንስጥ ብንል ለሁሉም ማዳረስ የማንችል ከመሆኑም በላይ ያለችንንም ዝቅተኛ የሥራ ተነሳሽነት መንፈስ ጨርሶ የሚያዳክምብን ስለሚሆን ኤች አይ ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ የበሽታውን ስርጭት በከፋ ሁኔታ ስለሚያባብሰው ወደማንወጣው የድህነት አዙሪት ውስጥ እንገባለን፡፡

<u>የተወሰደ አማራጭ</u>

ለኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ የምናገኘውን የብድርና እርዳታ ገንዘብ በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ ላይ እንዲውል በማድረግ የተረጅነት ስሜት እንዲቀንስ የማድረግ አሠራርን መዘርጋት የተሻለ አማራጭ ነው፡፡

3. <u>በገጠር የሚሠማሩ መያዶች ቁጥር አነስተኛ መሆን</u>

እስካሁን ባለው ልምድ መያዶች የክልሉን ልማት ለማፋጠን የሚሠሩበትን አካባቢ ቀድመው በመምረጥና በመወሰን የሚመጡ በመሆናቸው ይዘውት የሚመጡትን ሀብት እንዳይመለስ ከመስጋት አንፃር ወደ ገጠር ለመግፋት አልተሞከረም፡፡ ይህም በሚመርጧቸው ከተሞች ቁጥራቸው እንዲበራከት በር ከመክፈቱም በላይ የገጠሩ አካባቢ በመሠረተ ልማት ያልተደገፈ በመሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚስብ እንዳይሆን ስላደረገው በገጠሩ አካባቢ ለመቆየትና ሥራን ለማከናወን ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ የቫይረሱን የመከላከል እንቅስቃሴ ከተማ ላይ ያተኮረ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ይህም የሀገራችን ህብረተሰብ በብዛት የሚገኝበትን የገጠሩን አካባቢ እንዲረሳ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በርካታው የገጠር ኅብረተሰብም የቫይረሱን እንቅስቃሴ ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ተሳታፊ ባለመሆኑ የጥረቱ ውጤታማነት ጥያቄ ላይ ወድቋል፡፡

## የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት

የኤች አይ ቪ/ኤድስን ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚደረጉ ጥረቶች ከተማ ላይ ያተኮሩ በመሆኑና የገጠሩ ኅብረተሰብ ኤች አይ ቪ/ኤድስን የከተሜው ብቻ ችግር አድርጎ እንዲያይ ከማድረጉም በላይ የገጠሩ ኅብረተሰብ ሁለገብ እንቅስቃሴ እንዳይካተት ስለሚያደርግ ቫይረሱን የመከላከል ተግባር ውጤታማ እንዲሆን አያስችልም፡፡ ይህም የቫይረሱ ስርጭት እንዲባባስ ከማድረጉም አልፎ ወደ ባሰ የችግር አዙሪት ስለሚያስገባን ከድህነት ለመላቀቅ የምናደርገው ጥረት ጥያቄ ላይ ይወድቃል፡፡

## የተወሰደ አማራጭ

በገጠሩ አካባቢ ሀገር በቀል ድርጅቶች፣ ኅብረተሰብ አቀፍ ተቋማት ላይ አተኩሮ መስራትና በሰው ኃይልም ሆነ በማቴርያል የተጠናከሩ እንዲሆኑ ማድረግ፣

## 4. የሰው ኃይል ያለመሟላትና ከሥራ የመልቀቅ ችግር

ሴክሬታሪያቱ በተቋቋመበት ወቅት የወረርሽኙን አስከፊነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተከተልነው አጣዳፊ ሂደት ድርጅቱን በአነስተኛ የሰው ኃይል ማዋቀርና በጊዜያዊነት ሥራ ላይ የማዋል ሁኔታ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ችግሩን በዘለቄታዊነት ከመቅረፍ አንፃር የሴክሬታሪያቱ የሰው ኃይል አደረጃጀት የመዋቅር ጉዳይ ለረጅም ጊዜ ሳይታይ በመቆየቱ የሰው ኃይሉ በሚፈለገው መጠን ሳይሟላ ከመቆየቱም በላይ ያሉትንም ሠራተኞች ጥቅማቅጥሞችና የሥራ ዋስትና ማስጠበቅ ሳይቻል ቆይቷል፡፡

በዚህም የተነሳ የሥራውን ጫና ያበራከተው ሲሆን ውጤታማነቱን የገታው ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ የሆነ የሠራተኛ የመልቀቅ ችግር አጋጥሟል፡፡ የመዋቅሩም ጉዳይ እልባት ባለማግኘቱ የተፈለገውን የሠው ኃይል በሥራ ላይ ለማሰማራት አልተቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሠራው ሥራ ውጤታማነቱ በሚፈለገውና በሚታሰበው መልኩ እንዲሄድ አላደረገም፡፡

## የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት

- ሥራውን በሚፈለገው ጥፍነትና ጥራት ለማከናወን ያለመቻል፣
- የጅምር ሥራዎች መቋረጥና መጓተት፣

- ኤች አይ ቪ/ኤድስ የመከ/የመቆ/እንቅስቃሴ የተገደበ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## የተወሰደ አማራጭ

የመዋቅሩን ጉዳይ እልባት ማስገኘትና የሚጠይቀውን የሠው ኃይል በአዲስ ቅጥር መፈፀም፣ የሠራተኛውንም ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከበሩ ማድረግ፡፡

# 9. የማስፈፀሚያ ስልቶች/ስትራቴጂዎች/

1. የተለያዩ ረጂ ድርጅቶችን በማፈላለግ በፕሮጀክት ያልታቀፉ ወረዳዎች እንዲካተቱ ማድረግ
2. የክልል የዞንና የወረዳ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያ ጽ/ቤቶችን አቅም ለማጎልበት የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት
3. በጽ/ቤቱ ባለሙያዎች በማስገምገም ብቁ የሆኑትን ፕሮጀክቶች ለውሳኔ በቀጥታ ለሥራ አመራር ቦርዱ ማቅረብ
4. የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ ትኩረት በመስጠት በዕቅድ አካቶ ለመስራት የስራው ባለቤት/focal person/ እንዲመደቡለት ሴክሬታሪያቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች ማስተዋወቅና ግንዛቤ እንዲጨብጡ የማድረግ ሥራ፣ የስራ ዝርዝር መመሪያ በማዘጋጀት ማስተዋወቅና የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት፣ የተጠናከረ ክትትልና ግምገማ ሥራ ማካሄድ፣
5. በሕብረተሰብ አቀፍ ተቋማት ዙሪያ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስና መደገፍ፣
6. የባህሪይ ለውጥ ለማስገኘት የሚያስችሉ ስልጠናዎች የሕብረተሰብ አቀፍ ተቋማትን በመሠልጠን በእነርሱ አማካኝነት ወደ ሕብረተሰቡ እንዲወርድ ማድረግ
7. አካባቢያዊ ተኮር የሆኑና ሁሉም ሕብረተሰብ ሊረዳው የሚችል የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት ማቴሪያሎች ማዘጋጀትና በስፋት ማድረስ እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችን በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ በስፋት መጠቀም፣
8. ኮንዶም በሕብረተሰቡ ተቀባይነት እያገኘ እንዲሔድ የአመለካከትና የባህሪይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የመረጃ ትምህርትና ስርፀት ስራዎችን ማከናወን በፀረ ኤድስ ክበባትና ማህበራት በኩል የኮንዶም አቅርቦትና ስርጭት ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ በቀጣይነትና በብዛት እንዲደርስ ማድረግ እንዲሁም የትምህርትና ቅስቀሳ ስራ በስፋት ማከናወን፣
9. የአባለዘር በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የግል የጤና ተቋማትን ማጠናከርና መደገፍ፣
10. በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት በመንግሥት፣ መንግስታዊ ባልሆኑና በግል ድርጅቶች እንዲከናወን መደገፍና ለጤና ተቋማት የስልጠናና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣

11. በክልሉ ለሚገኙ የደም ባንክ ማዕከላት የገንዘብና የስልጠና ድጋፍ በመስጠት ሕብረተሰቡ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ የፀዳ የደም አቅርቦት እንዲያገኝ ማድረግ።
12. ከእናት ወደ ሕፃን የሚተላለፈውን የኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ ለመከላከል እንቅስቃሴ የሚያካሄዱ ሆስፒታሎችን በገንዘብና ስልጠና መደገፍ
13. ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ህፃናት የሙያ ስልጠና እንዲያገኙና በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች እንዲሰማሩ ማድረግ፣
14. በቀበሌ ደረጃ የሚሰጠው የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት በመረጃ በተደገፈ ፍላጎት ላይ የተመሠረተና ዘላቂነት ያለው እንዲሆን ማድረግ፣
15. ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ህፃናት በማህበር እንዲደራጁ ቅስቀሳና ትምህርት በሰፊው ማካሄድ፣
16. ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ሕፃናት ሰብአዊ መብታቸው እንዲከበርና እነርሱም የሌላውን እንዲያከብሩ የሚያስችል ህጋዊ ማዕቀፍ በፍትህ አካላት እንዲዘጋጅ ማድረግ
17. የጥናትና ምርምር በኤች አይ ቪ/አድስ ላይ እንዲካሄድ የጋራ ኮሚቴ እንዲንቀሳቀስ ማድረግና መመሪያዎችን ማዘጋጀት
18. በእቅድ የተያዙ የፀረ ኤድስ ስራዎች በወቅቱ እንዲፈፀሙ የተጠናከረ የክትትልና የግምገማ ስርዓት በየደረጃው መዘርጋት፣

# 10. የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት የ1996-1998 የሥራ መርሐ ግብር

| ተቁ | አበይት ተግባራት | መለኪያ | ብዛት | ፈፃሚ አካል | የጊዜ ሠሌዳ | | | የሚጠይቀው ወጪ | የበጀት ምንጭ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1996 | 1997 | 1998 | | | |
| 1 | **የነባር ወረዳዎች የሚቀጥል እንቅስቃሴ** | | | | | | | | | |
| | ➢ የኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ኤድስ ኘሮግራም ለታቀፉ ወረዳዎች የቀበሌ ድጋፍ ፈንድ | ቁጥር | 18 | | 18 | 18 | | 30532000.00 | ኢምሣፕ | |
| | ➢ አክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ በታቀፉ ወረዳዎች | ቁጥር | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4003125.00 | አ.ኤ.ኢ. | |
| 2 | **ወረዳዎችን ማስፋፋት** | | | | | | | | | |
| | ➢ ኢምሣፕ /EMSAP/ | ቁጥር | 27 | የክልል ሴክሬታሪያት | 12 | 15 | አዲስ አይጨምርም ያለው ይቀጥላል | 21488000.00 | አምሣፕ | |
| | ➢ አኤኢ (Action AID) | ቁጥር | 6 | የክልል ሴክሬታሪያትና አ.ኤ.ኢ | 3 | 3 | አዲስ አይጨምርም ያለው ይቀጥላል | 2401875.00 | አ.ኤ.ኢ | አንድ ወረዳ በሁለት/ ከዚያ በላይ ኘሮጀክት ሊታቀፍ ይችላል |
| | ➢ ሲዳ ሰርድፕ/SIDA SARDP/ | ቁጥር | 16 | የክልል ሴክሬታሪያትና ሲዳ | 16 | - | አዲስ አይጨምርም ያለው ይቀጥላል | 12000000.00 | ሲዳ | |
| | ➢ በሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች በኘሮጀክት ሊታቀፉ የሚችሉ | ቁጥር | 10 | የክልል ሴክሬታሪያትና የተለያዩ ለጋሾች | 4 | 3 | 3 | 6600000.00 | UNICEF | በጀት የሚለቀቀው ኘሮጀክቶች እየተገመገሙ ነው |
| 3 | **ኘሮጀክት ምዘናና ክትትል ማድረግ** | | | | | | | | | |
| | ➢ ምዘና ተደርጎባቸው ምላሽ የሚሰጣቸው የኘሮጀክቶች ብዛት | ቁጥር | 300 | የክልል የዞን የወረዳ የሴክሬታሪያት | 300 | 300 | 300 | | | |
| | ➢ ምዘና ከተደረገባቸው 50% የሚሆኑት ገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ | ቁጥር | 150 | የሥራ አመራር ቦርድ | 50 | 50 | 50 | 30,000,000.00 | 6513416 ዩኒሴፍ | |
| | ➢ የኘሮጀክት ጥናትና አቀራረብ ስልጠና የሚያገኙ ድርጅቶች | ቁጥር | 150 | የክልል ሴክሬታሪያት | 50 | 50 | 50 | 301101.00 | 170001 ኢምሳፕ 131100 አኤኢ | ለ5 ቀናት ያክል ከድርጅቶች አንድ አንድ ሰው ይሰለጥናል |
| | **ንዑስ ድምር** | | | | | | | 100,726,101.00 | | |

| ተቁ | አበይት ተግባራት | መለኪያ | ብዛት | ፈፃሚ አካል | የጊዜ ሠሌዳ | | | የሚጠይቀው ወጪ | የበጀት ምንጭ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1996 | 1997 | 1998 | | | |
| 4 | **<u>የመንግስት ሴክተሮችን የሥራ እንቅስቃሴ ተሳትፎ ማሳደግ(Mainstreaming)</u>**<br>➢ Mainstreaming መመሪያ ማዘጋጀትና ማሠራጨት | | | የክልል ሴክሬታሪያት | | | | 40000 | | |
| | ➢ የተሳታፊ ድርጅቶችን ቁጥር ከ20 ወደ 60 ማሳደግ | ቁጥር | 42 | መንግስታዊ አካላት | 40 | - | - | - | - | |
| | ➢ ድርጅቶቹ በሚያቀርቡት ዓመታዊ ዕቅድ መሠረት በጀት መፍቀድ | ቁጥር | 42 | መንግስታዊ አካላት | 42 | 42 | - | 20,979,312 | ኢ.ምማኘ | |
| | ➢ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ተጠሪ ሙያተኞችን ቁጥር ከ18 ወደ 60 ከፍ እንዲል ማድረግ | ቁጥር | 42 | መንግስታዊ አካላት | 42 | 60 | - | - | | |
| | ➢ ከመንግስት አካላት ለሚመጡ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ተጠሪ ሙያተኞች ሥልጠና መስጠት | ቁጥር | 60 | የክልል ሴክሬታሪያት | 42 | 20 | | 40000 | ኢ.ምማኘ 10000<br>አ.ኤ.ኢ 30000 | |
| | ➢ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሥርጭትን የሚያባብሱ ሁኔታዎችን ለመቀነስ የጫት ቤቶች፣ ሕገወጥ የቪዲዮ ቤቶችና ሕገ ወጥ የዳንስ ምሽቶች እንዲዘጉ የንግድና ኢንዱስትሪ፣ የፍትህ ቢሮና የጎጂ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ እንዲጠናከሩ ድጋፍ ማድረግ | ቁጥር | 3 | የክልል ሴክሬታሪያትና የፍ ትህ፣የንግደና ኢንዱስ ትሪ ባህል አስወጋጅ ኮሚቴ | | | | 60000 | ኢ.ምሳኘ | |
| 5 | **<u>በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ዙሪያ የሕብረተሰብ አቀፍ ተቋማት ተሣትፎ ማሳደግ</u>**<br>110 የኤች አይ ቪ/ኤድስ ክበባትንና ማህበራትን ማጠናከር | ቁጥር | 110 | የወረዳዎችና ዞን ሴክሬታሪያት | 40 | 35 | 35 | 792,000 | ኢ.ምሳኘ | |
| | ➢ 55 አዳደስ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ክበባት ማህበራት እንዲመሠረቱ ማድረግ | ቁጥር | 55 | ወረዳዎች ዞን ሴክሬታሪያት | 30 | 10 | 10 | - | - | በዞን 10 የሚ ሆኑ ይጠናከራሉ<br>በዞን 5 የሚሆኑ ይመሠረታሉ |
| | ➢ 660 የሕብረተሰብ አቀፍ ተቋማት ማህበራት ክበባትና በቤት ለቤት ድጋፍና እንክብካቤ ማሰልጠን | ቁጥር | 660 | የክልል ሴክሬታሪያት እና ጤና ቢሮ | 220 | 220 | 220 | 330,000 | ኢ.ምማኘ | በዞን 220 |
| | ➢ በቀበሌ ደረጃ ቢያንስ አንድ እድር ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አካቶ እንዲሰራ መደገፍ/የቴክኒክ ድጋፍ/ | ቁጥር | 3224 | የወረዳ ሴክሬታሪያት | 1612 | 1612 | - | | | |
| | **ንዑስ ድምር** | | | | | | | **22,241,312.00** | | |

| ተቁ | አበይት ተግባራት | መለኪያ | ብዛት | ፈፃሚ አካል | የጊዜ ሠሌዳ | | | የሚጠይቀው ወጪ | የበጀት ምንጭ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1996 | 1997 | 1998 | | | |
| 6 | **የክልል የዞንና የወረዳ ሴክሬታሪያትን ማጠናከር** | | | | | | | | | |
| | ➢ 33 የወረዳ ጽ/ቤቶችን የቢሮ ቁሳቁስ ማሟላት | በቁጥር | 33 | የክልል ሴክሬታሪያት | 15 | 18 | | 330,000.00 | 60000 አኤኢ<br>27000 ኢምሣኘ | |
| | ➢ ለ45 የወረዳ ጽ/ቤቶችን የሞተር ብስክሌት ማሟላት | በቁጥር | 45 | የክልል ሴክሬታሪያት | 20 | 40 | 16 | 540,000.00 | ኢምሣኘ | በኢምሳኘና በአክሽን ኤይድ ለታቀፉ ወገዳዎች ብቻ |
| | ➢ ለ13 የዞን ጽ/ቤቶችና ለክልል ሴክሬታሪያት ኮምፒዩተር አገልግሎት እንዲኖራቸው ማድረግ | በቁጥር | 13 | የክልል ሴክሬታሪያት | 13 | - | - | 195,000.00 | 45000 ባክኣኘ ኢኒሽቲቭ<br>150000 ኢምሳኘ | |
| | ➢ የክልል ሴክሬታሪያት 2 መኪናዎች እንዲኖሩት ማድረግ<br>የሴክሬታሪያቱን አደረጃጀት ማጠናከር | በቁጥር | 2 | በለጋሽ ድርጅቶች | 1 | 1 | - | 600,000.00 | 300000 አኤኢ<br>300000 አምሳኘ | |
| | ➢ ዳታ ቤዝ ማኔጅመንትና የዌብ ሳይት ሲስተምን መዘርጋት | | | በለጋሽ ድርጅቶች | | | | 1,235,520.00 | ባክአኘ ኢኒሽቲቭ | (144000 Euro) |
| 7 | **በሕብረተሰቡ ዘንድ የባሕሪ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ** | | | | | | | | | |
| | ➢ የባሕሪ ለውጥ አምጪ የአሠልጣኞች ስልጠና ለ250 ሰዎች መስጠት | ቁጥር | 250 | የክልል ሴክሬ.<br>ጤና ቢሮ | 100 | 100 | 50 | 342,500.00 | ኢምሳኘ | በዞን 22 የሚሆኑ ይሠለጥናሉ |
| | ➢ የሥርዓት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ የመልዕክት አቀራረጽና የመረጃ የመረጃ ሥርፀት እንዲኖር ማድረግ | | | የክልል ሴክሬ.<br>አ.ኤ.ኢ. | | | | | | |
| | ➢ የመልዕክት አቀራረጽና የመረጃ ሥርፀት መመሪያ ማዘጋጀት | በቁጥር | 1 | | 1 | | | 260,000.00 | አኤኢ | |
| | ➢ የመሪነት ሚናን የተሟላ ለማድረግ 339 መሪዎችን ማፍራት | በቁጥር | 339 | የዞን የወረዳ ሴክሬታሪያት | 113 | 113 | 113 | 693,255.00 | ኢምሳኘ | በወረዳ 3 ከተለያዩ የኃይማኖት የኅብረተሰብ አቀፍ ተቋማትና የፖለቲካ አካላት |
| 8 | **በክልሉ ውስጥ የኮንዶም ስርጭትንና አጠቃቀምን ማሻሻል** | | | | | | | | | |
| | ➢ የኮንዶም ተጠቃሚውን ሕብረተሰብ በ5% ከፍ ማድረግ | በፐርሰንት | 5 | በተለያዩ ድርጅቶች<br>ክበባት ማህበራት | 1 | 2 | 2 | | | |
| | **ንዑስ ድምር** | | | | | | | **4,196,275.00** | | |

| ተቁ | አበይት ተግባራት | መለኪያ | ብዛት | ፈፃሚ አካል | የጊዜ ሠሌዳ | | | የሚጠይቀው ወጪ | የበጀት ምንጭ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1996 | 1997 | 1998 | | | |
| 9 | <u>**የአባላዘር በሽታዎች ሕክምናና ቁጥጥር እንዲሻሻል ማድረግ**</u><br>➢ በጤና ቢሮ የሚካሄዱትን የአባላዘር ሕክምናና ቁጥጥር ለሚያስፈልግ ሥልጠና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ | ቁጥር | 169 | የክልል ሴክሬታሪያትና ጤና ቢሮ | 94 | 75 | - | 1,922,194.00 | ኢምሳኘ | የጤና ቢሮ የጋራ ስምምነት ያስፈልጋል |
| 10 | <u>**በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት በክልሉ እንዲዳረስ ማድረግ**</u><br>➢ በ100 ወረዳዎች የቪሲቲ አገል/ ማስጀመር | በቁጥር | 100 | የክልል ሴክሬታሪያትና ጤና ቢሮ | 40 | 30 | 30 | - | - | ገንዘቡ በኘሮጀክት የመንግስት ድርሻ ላይ ተመልክቷል በእያንዳንዱ ወረዳ ይቋቋማል ስለዚህ ወረዳዎች ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው |
| | ➢ በ100 ወረዳዎች የቪሲቲ አገልግሎት እንዲሠጥ ለማድረግ የምክር አገልግሎትና የላብራቶሪ ቴክኒሽያን ሥልጠና መስጠት | በቀጥር | 200 | የክልል ሴክሬታሪያትና ጤና ቢሮ | 80 | 60 | 60 | 315,000.00 | 100000 አኤኢ | |
| | ➢ በየቀበሌው ሦስት የሚሆኑ የሕብረተሰብ አቀፌ ተቋማት ምክር አገልግሎት እንዲሰጡ የምክር አገልግሎት አሠጣጥ ሥልጠና መስጠት | በቁጥር | 9672 | የክልሉ የዞን፣የወረዳ ሴክሬታሪያትና ጤና ቢሮ | 3224 | 4836 | 1612 | 4,613,490.00 | 4613490 ኢምሳኘ | 1392 ሰው በሲዳ ይሠለጥናል በከፍተኛ ደረጃ ኃላፊነቱ የዞንና የወረዳ ሴክሬታሪያት ነው<br>አኤኢ 957 ሠወ ይሠለጥናል |
| 11 | <u>**የክልሉ ታካሚ ሕብረተሰብ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ የነፃ የደም አቅርቦት እንዲያገኙ ማድረግ**</u><br>➢ በክልሉ ሆስፒታሎች የተሻሻለ የደም ባንክ አቅርቦት እንዲኖራቸው ድጋፍ ማድረግ | በቁጥር | 7 | በክልል ሴክሬታሪያትና ጤና ቢሮ | 4 | 3 | | 349,134.00 | ኢምሣኘ | |
| 12 | <u>**በክልለ ውስጥ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ከእናት ወደ ሕፃን የሚተላለፍበትን መጠን መቀነስ**</u><br>➢ የጎንደር ሕክምና ኮሌጅ የተጀመረውን የPMTCT አገልግሎት ማጠናከር | | 1 | | 1 | | | | ዩኒሴፍ | |
| | ➢ በክልሉ 2 ሆስፒታሎች ተጨማሪ የPMTCT አገልግሎት እንዲከፈት ድጋፍ ማድረግ | በቁጥር | 3 | የክልሉ ሴክሬታሪያት እና ጤና ቢሮ | 3 | | | 353,122.00 | ኢምሣኘ | በዩኒሴፍ ኘሮጀክት ከተቀመጠ ው በጀት ውስጥ የተካተተ |
| | **ንዑስ ድምር** | | | | | | | 7,552,940.00 | | |

| ተቁ | አበይት ተግባራት | መለኪያ | ብዛት | ፈፃሚ አካል | የጊዜ ሠሌዳ | | | የሚጠይቀው ወጪ | የበጀት ምንጭ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1996 | 1997 | 1998 | | | |
| 13 | **<u>በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎትን ማጠናከር</u>**<br>➢ 8 ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ሕፃናት ማህበር እንዲቋቋሙ | ቁጥር | 8 | የዞን ሴክሬታሪያት | 8 | 11 | 11 | 170,000.00 | 170000 አኤኢ | በጀቱ በስሩ የተጠቀሱትን ያጠቃልላል/ከአምሳኝ የሚሠጠውን አኘሬዛል ውስጥ ተካቷል |
| | ➢ 3 ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ሕፃናት ማህበርን መደገፍ | በቀጥር | 3 | የዞን ሴክሬታሪያት | | | | | | በዞን አንድ ይቋቋማል |
| | ➢ በክልሉ የሚገኙ 20% የሚሆኑ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወላጅ አልባ ሕፃናት በገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ ራሳቸውን እንዲደግፉ ማድረግ | በፐር ሰንት | 20 | የዞን የወረዳ ሴክሬታሪያት | 10 | 5 | 5 | | | |
| 14 | **<u>ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ሕፃናት ሰብአዊ መብት እንዲከበርና እንዲያከብሩ ማድረግ፣</u>**<br>➢ በፌደራል ደረጃ የኤች አይ ቪ/ኤድስና የሰብአዊ መብት አከባበር ላይ የሚመጣውን ረቂቅ ሕግ ለክልሉ ሕብረተሰብና ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች ማስተዋወቅ | | | በየደረጃው ያሉ የሴክሬታሪያትና የፍትህ አካላት | X | X | | 207,892.00 | 30000 አኤኢ<br>177892 ኢምሣኝ | በክልል፣በዞን በወረዳ፣በቀበሌ ደረጃ ይፈፀማል |
| 15 | **<u>በክልሉ ውስጥ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችን ማጠናከር፣</u>**<br>➢ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ በጥናትና ምርምር የሚሳተፉ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲበራቱ በክልል ደረጃ አንድ የመረጃ ማዕከል /Data base/ እንዲቋቅም ማድረግ | በቁጥር | 1 | የክልሉ ሴክሬታሪያት እና ጤና ቢሮ | X | | | 440,202.00 | 60000 አኤኢ<br>380202 ኢምሳኝ | |
| | **ንዑስ ድምር** | | | | | | | **818,094.00** | | |

| ተቁ | አበይት ተግባራት | መለኪያ | ብዛት | ፈፃሚ አካል | የጊዜ ሠሌዳ | | | የሚጠይቀው ወጪ | የበጀት ምንጭ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1996 | 1997 | 1998 | | | |
| 16 | <u>**የክልል፣ የዞን የወረዳ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ጽ/ ቤቶችን የማስፈፀም አቅም እንዲሻሻል ማድረግ**</u><br>➢ በፕሮጀክት ዝግጅት አመራር ሙያ 8 የክልል ሴክሬታሪያት 105 የወረዳ አስተባባሪዎችና 10 የዞን አስተባባ ሪዎችን ማሰልጠን | ቁጥር | 123 | የክልሉ ሴክሬታሪያት | 123 | | | 172,200.00 | 35000 አኤኢ<br>137200 ኢምሳኘ<br>22000 አኤኢ | በአማካኝ የ7 ቀናት ሥልጠና |
| | ➢ የአገር ውስጥ አውደ ጥናቶች ሥልጠ ናዎችና የልምድ ልውውጥ ማድረግ | ቁጥር | 45 | የክልሉ ሴክሬታሪያት | 15 | 15 | 15 | 120,000.00 | 98000 ኢምሳኘ<br>86000 አኤኢ | |
| | ➢ አለም አቀፍ አውደ ጥናቶች ሥልጠ ናዎችና የልምድ ልውውጥ ማድረግ | ቁጥር | 9 | የክልሉ ሴክሬታሪያት | 3 | 3 | 3 | 249,000.00 | 163000 ኢምሳኘ | |
| | ➢ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ ከሚሠሩ አጋር ድርጅቶች፣ የመንግስት ሴክተሮች ጋር የግንኙነት አውታርን ማጠናከር | | | በክልል ሴክሬታሪያት፣ አክሽን ኤይድና ሌሎች | | | | 90,000.00 | 90000 አ.ኤ.ኢ | |
| 17 | <u>**ክትትልና ግምገማ ማድረግ**</u> | ቁጥር | 4 | በሴክሬታሪያቱ በዞኖች | 4 | 4 | 4 | 490,000.00 | 245000 አኤኢ<br>245 ኢምሳኘ | በአመት አራት ጊዜ |
| 18 | <u>**የፕሮጀክት አስተዳደራዊ ወጪ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ**</u> | በቁጥር | 4 | በሴክሬታሪያቱና በዞኖች | | | | 9,463,598.00 | 362080 አኤኢ<br>5666842 መንግስት<br>3434676 ኢምሳኘ | |
| | **ንዑስ ድምር** | | | | | | | **10,584,798.00** | | |

<u>**ጠቅላላ ድምር**</u> <u>**146,119,520.00**</u>

## 11. የሠው ኃይል ዕቅድ

## ሀ. በመንግሥት

| ተቀ | የሥራ መደቡ መጠሪያ | አሁን ያለ | 1996 | 1997 | 1998 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሴክሬታሪያቱ ጽ/ቤት | | | | |
| | 1.1 ኃላፊ | 1 | - | - | - |
| | 1.2 ኤክዘኪዩቲቭ ሴክሬታሪ | 1 | - | - | - |
| | 1.3 የኘሮግራም ኦፊሰር | - | 1 | - | - |
| | 1.3.1 የግምገማና ክትትል ባለሙያ | - | 1 | - | - |
| | 1.3.2 የመረጃ ትንተናና ስርፀት ባለሙያ | - | 1 | - | - |
| | 1.4 የፋይናንስ ኦፊሰር | 1 | - | - | - |
| | 1.5 ሾፌር | 1 | - | - | - |
| | ን/ድምር | 4 | 3 | - | 7 |
| 2. | የኦኘሬሽንና ሥልጠና መምሪያ | | | | |
| | 2.1 መምሪያ ኃላፊ | 1 | - | - | |
| | 2.2 ሴክሬታሪ | - | - | - | |
| | 2.3 የድጋፍና ማኀ/አገልግሎት ባለሙያ | - | 1 | - | |
| | 2.4 የትምህርት ዝግጅትና ሥልጠና ባለሙያ | - | 1 | - | |
| | 2.5 የኦዶቪዥዋልና ህትመት ባለሙያ | - | 1 | - | |
| 3. | የዞን አስተባባሪ /በዞን አንድ/ | | | | |
| 4. | የወረዳ ባለሙያ / በወረዳ አንድ/ | | | | |
| | ን/ ድምር | 1 | 4 | 5 | 5 |
| | ጠቅላላ ድምር | 5 | 7 | 12 | 12 |

## ለ. በፕሮጀክት

| ተቀ | የሥራ መደብ | አሁን ያለው | 1996 | 1997 | 1998 | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክትትልና ግምገማ ኦፊሰር | 1 | - | - | - | 1 |
| 2 | አክሽን ኤይድ/ሲፓ/ፕሮጀክት ኦፊሰር | 1 | - | - | - | 1 |
| 3 | ረዳት/ፕሮጀክት ኦፊሰር | 1 | - | - | - | 1 |
| 4 | ረዳት ሂሣብ ሠራተኛ | 1 | - | - | - | 1 |
| 5 | ተንቀሳቃሽ ሂሣብ ሠራተኛ | - | 1 | - | - | 1 |
| 6 | የአክሽን ኤይድ መለሥተኛ ሂሣብ ሠራተኛ | 1 | - | - | - | 1 |
| 7 | ፕላኒግ ኦፊሰር | - | 1 | - | - | 1 |
| 8 | ፕሮግራም አድቫይዘር | - | 1/VSO/ | - | - | 1 |
| 9 | ዳታ ቤዝ ኦፊሰር | - | 1/VSO/ | - | - | 1 |
| | ድምር | 5 | **4** | - | - | 9 |

## 12. የፋይናንስ ዕቅድ

| | 1996 | 1997 | 1998 | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|
| ገቢ | 58996319.00 | 60400511.00 | 26722690.00 | 146119520.00 |
| ወጪ | | | | |
| ➢ መደበኛ | 56315597.00 | 59740511.00 | 26722690.00 | 142778798.00 |
| ➢ ካፒታል | 2680722.00 | 660,000.00 | - | 3340722.00 |
| | | | | |

በመንግስት የሚሸፈን የ53 ወረዳዎች፣ የ11 ዞን አስተባባሪዎች፣ 13 የክልል ሴክሬታሪያት ባለሙያዎች ደመወዝ 3,866,842.00 እና የሥራ ማስኬጃ 1,800,000.00 በድምሩ 5,666,842.00 ገንዘብ ከመንግሥት ይጠበቃል፡፡

## 13. ክትትልና ግምገማ

ማንኛውም የሥራ ዕቅድ ሲዘጋጅ በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ለሚከሰቱ ችግሮች በየጊዜው ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት ዕቅዱ በተቀመጠለት ጊዜ ተፈፃሚ እንዲሆን የማስፈፀሚያ ስልቶች ከወዲሁ መቀየስ አስፈላጊ ነው::

ከእነዚህ መካከል በሚከናወኑ ሥራዎች ላይ የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ሂደት መኖር አንዱ ስልት ነው:: ለዚሁ እንዲያመች የሥራ ዕቅዱን እንደአስፈላጊነቱ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በመለየትና የሥራ ክፍፍል በማድረግ የክትትልና የግምገማ ተግባራት ማከናወን አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አለ:: በዚሁ መሠረት ምንም እንኳን ሁሉም የልማት ሥራዎች በተያዘላቸው የማስፈፀሚያ ሀብትና የጊዜ ሰሌዳ እንዲከናወኑ የቅርብ ክትትልና ግምገማ የሚደረግባቸው ቢሆንም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በፕሮጀክት ደረጃ የተያዙ የፀረ ኤድስ ሥራዎች ከሚፈልጉት ድጋፍ አኳያ የተለየ ትኩረት ሊሠጣቸው ይገባል::

በክልሉ በተለያዩ ፈፃሚ አካላት በኤድስ ዙሪያ በዕቅድ ተይዘው የሚከናወኑ ተግባራት በትክክል መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ፣ የታቀደላቸውን አላማ በሚገባ መምታታቸውንና የተመደበላቸውም ውስን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ እንዲሁም ብኩንነትን ለማስወገድ ክትትልና ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ ነው::

ስለዚህ በሴክሬታሪያቱ አስተባባሪነት ከ1995-1998 በክልል በሴክተር መ/ቤቶች፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ታስቦ በቀጣይ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ የተጠናከረ ክትትል በማድረግ በየደረጃው በዕቅድ የተያዙት የፀረ ኤድስ ሥራዎችን በመገምገም የሚከሰቱ የአሰራር ማነቆዎች እንዲወገዱና የፀረ ኤድስ ሥራዎች በየበጀት ዓመቱ በተመደበላቸው ውድና ውስን ሀብት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሆነው የሚጠበቀውን ውጤት እንዲሰጡ ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል::

በየበጀት አመቱ በሴክሬታሪያቱና በሌሎች ፈፃሚ አካላት በኩል የሚደረገው የክትትልና የግምገማ ሥራ አስፈላጊነት ዝርዝር ሲታይ:-

1. በክልል ደረጃ በሚገኙ የሴክተር መ/ቤቶች በኤድስ ዙሪያ ሊተገበሩ በዕቅድ የተደገፉ ሥራዎች በተቀመጠላቸው ጊዜና የማስፈፀሚያ ሀብት እንዲጠናቀቁ፣
2. በፕሮጀክት የታቀፉትና በቀጣይ የሚታቀፉት ወረዳዎች ከተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚመደብላቸው በጀት እስከ ቀበሌ ድረስ በተዘረጋው የአደረጃጀት ሠንሰለት በመጠ ቀም ለማከናወንና በዕቅድ የተያዙ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥራዎች አፈፃፀምና የተደረገውን የገንዘብ ክፍያ ለማረጋገጥ፣
3. ለአበዳሪና ዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በተገባው ውልና ግዴታ መሠረት በዘርፉ የሚተገበሩ ተግባራትን የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን የሚገልፁ መረጃዎችን አጠናቅሮ ለማቅረብ፣

4. በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚሳተፉ አካላትና ሥራዎችን በሚከታተሉና በሚቆጣጠሩ ድርጅቶች መካከል የተቃና ግንኙነት እንዲፈጠርና የአሰራር ማነቆዎች እንዲወገዱ ለማረግ፣
5. በሚካሄዱ ሥራዎች አፈፃፀም ወቅት የሚከሰቱ ዋና ዋና ችግሮችን በመለየት በሚደረገው ግምገማና ውይይት የመፍትሔ ኃሳቦችንም በማመንጨት ወቅታዊ የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ለማስቻል፣
6. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከል ረገድ በበጀት ዓመቱ ተጀምረው በተጠናቀቁ ሥራዎች ላይ የማጠ ቃለያ ግምገማ በማድረግ የተገኘውን ውጤት በመገምገም ከሚገኘው ልምድ መነሳት በቀጣይ ለሚታቀዱ የልማት ሥራዎች የመነሻ ኃሳቦች እንዲፈጠሩ ያግዛል፡፡

በአጠቃላይ በማንኛውም መልኩ የኘሮጀክት/ ኘሮግራም ዕቅድ እስካለ ድረስ የክትትልና የግምገማ ሥራ አብሮ የሚታይና በኘላን ሂደት ውስጥ የመጨረሻው ዕርከን መሆኑን በመገንዘብ በቀጣይ በሴክሬታሪያቱ የሚካሄደው የክትትልና ግምገማ ሥራ ጉልህ ሚና ያለው በመሆኑ የአሰራር ስርዓት ተበጅቶለት መተግበር ይኖርበታል፡፡

በዚህ መሠረት የሚከተሉት የክትትልና የግምገማ የአሰራር ስርዓቶች ተግባራዊ ይሆናሉ የሚል እምነት ተይዟል፡፡

- በየበጀት ዓመቱ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርቶች በየሩብ ዓመቱ እንዲዘጋጁ ማድረግ፣
- አንድ ወጥ የሆነ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፆች በማዘጋጀት በሥራ ላይ ማዋል፣
- በክልሉና በዞን ሴክሬታሪያቶች ደረጃ በየሩብ ዓመቱ በአመት አራት ጊዜ የሪቪው ስብሰባዎች ይካሄዳሉ፡፡ ከነዚህ ስብሰባዎች በመካከል በአመት ሁለት ጊዜ የወረዳ አስተባባሪዎችም የሚሳተፉበት ይሆናል፡፡
- በዕቅድ የተያዙ የፀረ ኤድስ ሥራዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ በየሩብ ዓመቱ ሁለት ጊዜ የመስክ ጉብኝት በክልሉ ሴክሬታሪያት ደረጃ ይካሄዳል፡፡ ይህም ለሚከሠቱ የአፈፃፀም ችግሮች የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## 14. የተያዙ ታሳቢዎችና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች

### ታሳቢዎች/Assumptions/

1. በሴክሬታሪያቱ የተዘጋጀው መዋቅር ፀድቆ ጽ/ቤቱ በሰለጠነ የሰው ኃይል ስለሚሟላ የመፈጸም አቅሙ የተሻለ ይሆናል፣
2. ሴክሬታሪያቱ የመፈጸም አቅሙን ለማሳደግ በቢሮ ቁሳቁሶች ሊደራጅ ይገባል፣
3. ለአስፈፃሚና ለፈፃሚ አካላት የተለያዩ ስልጠናዎች ስለሚሰጡና የመፈጸም አቅማቸው ስለሚጨምር በዕቅድ የተያዙ ሥራዎች ይከናወናሉ፣
4. ኤች አይ ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠሩ በኩል መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑ በዕቅድ ለተያዙት የፀረ ኤድስ ሥራዎች በቂ የማስፈጸሚያ በጀት ከመንግስትና ከለጋሽ ድርጅቶች ይኖራል፣

5. በዕቅድ የተያዙ የፀረ ኤድስ ሥራዎችን ለመተግበር በአቅም ግንባታና ስልጠና ድጋፍ የሕብረተሰቡ የተሣትፎ ደረጃ ካለፉት አመታት የተሻለ ይሆናል፣
6. ባለፉት ሁለት ዓመታት ዕቅድ አፈጻጸም ወቅት የተገኙ ጠንካራ የሥራ ተሞክሮዎችና ልምዶች ለዚህ ዕቅድ በመነሻነት ያገለግላሉ፡፡
7. ፕሮጀክት ቀርፀው ለመንቀሣቀስ ፕሮፖዛል ለሚያቀርቡ ድርጅቶች የሚሰጠው ምላሽ የተቀላጠፈ ይሆናል፡፡
8. ከብሔራዊ ሴክሬታሪያት ጋር የሚኖረን ግንኙነት ይጠናከራል፣ እንዲሁም የገንዘብ ፍሰቱ የተስተካከለ ይሆናል፡፡
9. በአዲሱ አደረጃጀት መሠረት የወረዳዎች የመፈፀም አቅም ይጨምራል፣ አስተባባሪ ባለሙያዎችም በመንግሥት በጀት ይቀጠራሉ፡፡
10. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የመንግሥት ሴክተር መ/ቤቶች ከመደበኛ ሥራዎቻቸው በተጓዳኝ የፀረ ኤድስ ሥራን አካተው ያካሂዳሉ፡፡

## ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች

1. በክልል በዞንና በወረዳ ሴክሬታሪያቶች ደረጃ በዕቅድ የተያዙ ሥራዎች ማስፈጸሚያ የተያዘው በጀት በታቀደው መጠንና በወቅቱ ላይገኝ ይችላል፣
2. ሴክሬታሪያቱ የሚሳተፍባቸው ነገር ግን በዕቅድ ያልተያዙና ረዘም ላለ ጊዜ ባለሞያን ሊጠምዱ የሚችሉ ሥራዎች መኖር
3. ለኮንትራት ሠራተኞች የሚከፈለው የፕሮቪደንት ገንዘብና ሌሎች ጥቅማጥቅመች ጉዳይ እልባት አለማግኘቱ በቀጣይ የባለሙያ እጥረት ለያስከትል ይችላል፡፡
4. በኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ኤድስ ፕሮጀክት ከአንድ አመት ተኩል በኋላ ስለሚጠናቀቅ ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ ኤድስን የመከላከል ሥራ እንዴት ይቀጥላል? የሚለው ጥያቄ ሊያሳስብ ይችላል፡፡
5. አብዛኛዎቹ የመንግሥት ሴክተር መ/ቤቶች ወረዳዎችን ጨምረው በኤድስ ዙሪያ ለሚፈጽሟቸው ተግባራት በወቅቱ የሥራ መርሐ ግብር አዘጋጅተው ስለሚያቀርቡ በሽታውን ለመከላከል ከተለያዩ ምንጮች የሚመደበውን በጀት በወቅቱ መጠቀም አለመቻል፣
6. በተለያዩ ድርጅቶች ለሴክሬታሪያቱ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የፀረ ኤድስ ፕሮጀክት ዶክመንቶች ጥራት ስለማይኖራቸው በሚደረገው የምዘና ግምገማ ወቅት በርካታ ጊዜ ሊወስዱ ይችላሉ፡፡

# በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉ ሰነዶች

1. የአማራ ክልል የ2ኛው አምስት ዓመት/1993-1997/ የልማት የሰላምና የዲሞክራሲ መርሀ-ግብር /ህዳር 1995ዓ.ም./
2. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አገር አቀፍ የኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት /የ1993-1997ዓ.ም. መርሀ ግብር/ መጋቢት 1993ዓ.ም.
3. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ክልል አቀፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት /የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ የ5 ዓመት/1993-1997ዓ.ም./ረቂቅ መርሃ ግብር/ መስከረም 1994ዓ.ም.
4. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ኘሮጀክት የኘሮጀክት አፈፃፀም መመሪያ/ታህሣስ 1993 ዓ.ም./